# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት




**መጋቢት/ 2011 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


ማውጫ ........ i

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ /ድርሞ/ (Executive Summery) ........ I

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የሚመለከቱ ህጎች ማዘጋጀቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ I

2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በላብራቶሪ መርምሮ መመዝገቡን በተመለከተ፤ ........ I

3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን ስራ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር መኖሩን እና በመዋቅሩ የተቀመጠውን የሰው ሃይል ማሟላቱን በተመለከተ፤ ........ I

4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት /በዳታ ቤዝ/ የተደገፈ እና በግልፅ መረጃውን ለተገልጋዩ የሚያሳውቅበት የመረጃ ልውውጥ ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ II

5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን መኖሩን በተመለከተ፤ ........ II

6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱን በተመለከተ፤ ........ II

7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ III

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ፤ ........ III

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፀረ ተባይ ኬሚካል ሰራተኞች ደህንነት እንዲጠበቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ IV

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤ ........ IV

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት በቅንጅት መስራቱን እና የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን በተመለከተ፤ ........ IV

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ ........ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ ........ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ ........ 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት ........ 3

የዕፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት ........ 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ........ 6

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል ........ 6

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 7

የኦዲቱ ዓላማ ........ 7

ለከዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ........ 8

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 8

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........ 8

የኦዲት ወሰንና ዘዴ ........ 9

የዕፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የሥራ ፍሰት መግለጫ (System Description) ........ 10

ክፍል ሁለት ........ 11

የኦዲት ግኝቶች ........ 11

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የሚመለከቱ ህጎች ማዘጋጀቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ ........ 11

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በላብራቶሪ መርምሮ መመዝገቡን በተመለከተ ........ 12

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ቅሪት መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ መኖሩን በተመለከተ ........ 13

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማስታወቂያዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 15

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥን በተመለከተ ........ 16

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ ያላቸው መሆናቸውን በተመለከተ ........ 18

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን ስራ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር መኖሩን እና በመዋቅሩ የተቀመጠውን የሰው ሃይል ማሟላቱን በተመለከተ 21

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን ስራ በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት መኖሩን በተመለከተ ........ 24

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በተመለከተ ........ 25

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረጉን በተመለከተ ........ 28

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን መኖሩን ........ 36

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱን በተመለከተ ........ 37

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭትላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 39

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ ........ 41

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የመሸጡ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ 45

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ በተመለከተ ........ 47

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፀረ ተባይ ኬሚካል ሰራተኞች ደህንነት እንዲጠበቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 52

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 55

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልታሸገና መለያ ያልተደረገበትን ፀረ ተባይ ኬሚካል ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 56

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 60

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን መከታተል እና መቆጣጠሩን በተመለከተ........ 62

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የተሰራላቸው መሆኑን በተመለከተ ........ 64

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 66

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠቱን እና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ ........ 69

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት በቅንጅት መስራቱን እና የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን በተመለከተ ........ 70

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ቆጠራ በማድረግ መወሰድ ያለበትን መነሻ ሀሳብ ማዘጋጀቱን እና ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረቡን በተመለከተ ........ 72

ክፍል ሦስት ........ 74

የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion) ........ 74

ክፍል አራት ........ 78

የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Audit Recommendation) ........ 78

አባሪ 1 የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር ........ i

አባሪ 2 የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት ........ ii

አባሪ 3 ........ vi

በናሙና የታዩ የከተማ መስተዳደሮች፣ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች እና በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ዝርዝር ........ vi

# የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ /ድርሞ/ (Executive Summery)

የክዋኔ ኦዲቱ አላማ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓት በተመለከተ ስራውን ለማስፈፀም የወጣውን አዋጅ መሰረት በማድረግ ደንብ፣ መመሪያ እና እስታንዳርድ በማውጣት በብቃት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ በማድረግ በተገቢው ሁኔታ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱንና የተዘረጋው የአሰራር ስርዓት ተፈፃሚ መደረጉን ለማረጋገጥ እና ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን ሲሆን ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘ የአሰራር ችግሮችን ለይቶ በማውጣት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቅነትን ለማስፈን ሲሆን በዚህ መሰረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የሚመለከቱ ህጎች ማዘጋጀቱንና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፤**
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደር እና ቁጥጥር በተመለከተ አዋጅ ያለ ሲሆን ስራውን ሊያሰሩ የሚያስችሉ ደንብ፣ መመሪያና እስታንዳርድ አለመዘጋጀቱ፣ እንዲሁም ደንብ እንዲወጣ ለበላይ አመራሩ ጥያቄ ቢቀርብም ቶሎ ምላሽ አለመሰጠቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡
2. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በላብራቶሪ መርምሮ መመዝገቡን በተመለከተ፤**
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡና ወደ ውጪ ሀገር በሚወጡ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ላይ አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የላብራቶሪ አገልግሎት ባለመኖሩ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው በላብራቶሪ ተመርምሮና ተረጋግጦ እንደማይመዘገብና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአሁኑ ሰዓት እየተመዘገቡ ያሉት እንዲሁ ዶክመንት /ወረቀት/ በማየት ብቻ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
3. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን ስራ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር መኖሩን እና በመዋቅሩ የተቀመጠውን የሰው ሃይል ማሟላቱን በተመለከተ፤**
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- የፀረ-ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር እና የሰው ሃይል በተደራጀ መልኩ አለመኖሩና ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑ እንዲሁም መዋቅሩ

ከፌደራል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ የተናበበ አለመሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት እንደሌለ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

4. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት /በዳታ ቤዝ/ የተደገፈ እና በግልፅ መረጃውን ለተገልጋዩ የሚያሳውቅበት የመረጃ ልውውጥ ማድረጉን በተመለከተ፤**
   - ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች፣ ከኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ከአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች እና በዘርፉ ስራ ከተሰማሩ አካላት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ደካማ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በእያንዳንዱ የፀረ ተባይ የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አጠቃቀማቸውን በሚመለከት ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ወይም በዳታ ቤዝ የተደገፈ መረጃ እንደሌለ እና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ እና በተገቢው ሁኔታ እንዳልሰራ ለመረዳት ተችሏል፡፡

5. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን መኖሩን በተመለከተ፤**
   - ✓ እንደ ሀገር ስለ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጠቀሜታ፣ በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ስለሚያስከትለው ጉዳት እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አስተማሪ የሆኑ መልዕክቶች የሚተላለፉበት የሚዲያ ሽፋን አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋት እና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ጎጅ ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን እራሱን የቻለ የአየር ሰዓት ተሰጥቶት በሚዲያ እንዲተላለፍ አለመደረጉ፤ ለዘርፉ እንደ ሀገር ትኩርት ያልተሰጠው መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

6. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱን በተመለከተ፤**
   - ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፣ ከጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ ከብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ሚኒስቴር የተውጣጡ እና የተዋቀሩ የቦርድ አባላት

እንደሚኖሩት ቢገለፅም ቦርዱ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ወደ ስራ አለመግባቱና በተወሰነለት ጊዜም አለመሰብሰቡን ለመረዳት ተችሏል፡፡

7. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤**
   - ✓ በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ የምርት መለያ ቁጥር 0001036360 እና 0001036401 በ17/10/2012 እና በ25/02/2012 ተመርቶ በ17/10/2014 እና በ25/02/2014 ከ7 ወር እስከ 1 ዓመት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት 19,790 (አስራ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና) ኪሎ ግራም ዳይሜቶኤት ቴክኒካል /Dimethoate Technical/ ጥሬ ዕቃ በመጠቀም 28,000 /ሀያ ስምንት ሺህ/ ሊትር ዳይሜቶኤት 40% ኢ.ሲ እና 6,000 (ስድስት ሺህ) ሊትር ዳይሜቶኤት 40% ዩ.ኤል.ቪ. በማምረት ለህብረተሰቡና ለአርሶ አደሩ በሽያጭ መልኩ መሰራጨቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ በኮንትሮባንድ የሚገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸው እና ህብረተሰቡ ከህገ ወጥ ነጋዴዎች ገዝተው ምንጫቸው ያልታወቁ እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ የሚረጩበት ሁኔታ መኖሩ ነገር ግን ይህን ችግር ለመቆጣጠር የሚያስችል የተቀናጀ የክትትል ስርዓት አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

8. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድን በተመለከተ፤**
   - ✓ በ9 ክልሎችና በ1 ከተማ መስተዳደር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው 928,509.31 ኪ/ግ ዲዲቲ መኖራቸው፤
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ለብቻቸው በአግባቡ መዝግቦ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው እና በየቦታው በተበታተነና ባልተደራጀ መልኩ እንደሚገኙ በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገዱበትን ስርዓት አለመዘርጋቱ እና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር

አለመቻሉን እኒዲሁም 1,432,074.5 **ሊትር** የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

9. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፀረ ተባይ ኬሚካል ሰራተኞች ደህንነት እንዲጠበቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤**
   - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብሮች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ምንም ዓይነት የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆችን እንደማይጠቀሙ፣ አርሶ አደሮቹ በአዝርት፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ሲረጩ፣ የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆችን አለመጠቀማቸው፣ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ድርጅቶች፣ የመንግስት መ/ቤት የመጋዘን ሰራተኞች፣ የዩኒየኖችና የማህበራት የፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝን ሰራተኞች፣ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅት ሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆች እንደማይቀርቡላቸውና ያለውንም እንደማይጠቀሙ እና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንዳላደረገ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

10. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤**
    - ✓ በኳራንቲን ጣቢያዎች በአካል በመገኘት በቂና ተከታታይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የፅሁፍ ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑ፤
    - ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሕገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝውውርን በሚመለከት ለኦሮሚያ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ የፅሁፍ ግብረ መልስ ቢሰጥም በፀረ ተባይ ኬሚካሎች እስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት ድንገተኛና ወቅታዊ በሆነ ጉዳይ ድጋፍና ክትትል ከማድረግ ውጭ በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትልና ቁጥጥር እንዳላደረገላቸው እና የፅሁፍ ግብረ መልስ እንዳልሰጣቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

11. **ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት በቅንጅት መስራቱን እና የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን በተመለከተ፤**
    - ✓ በ2009 በጀት አመት ህገ- ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካል ቁጥጥርን አጠናክሮ ለመስራት ከኦሮሚያ፣ ከትግራይ፣ ከአማራ እና ከደቡብ ብ/ብ/ ህዝቦች ብሄራዊ መንግስታት እና

ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ጋር የመግባቢያ ስነድ ለመፈራረም ታቅዶ አለመከናወኑ፤

- ✓ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች መሰረት፡- በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ጎጅ ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን እና እንደ ሀገር ለዘርፉ ትኩረት ካለመሰጠቱ አንፃር የሚመለከታቸውን ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ስራው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን በቅንጅት አለመሰራቱና የመግባቢያ ሰነድ /የጋራ እቅድ/ እንዳልተፈራረመ ለመረዳት ተችሏል፡፡

# ክፍል አንድ

***መግቢያ***

1. የግብርና ሴክተር በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስኮች የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማድረግ መንግስት የግብርናና የገጠር ልማት ፓሊሲና ስትራቴጂ ቀርፆ ተግባራዊ በማድረግ ውጤት እያስመዘገበ ሲሆን በሴክተር የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካትና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የግብርና ሴክተር ፓሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን የማስፈፀም፣ ክልሎችን የመደገፍና የማስተባበር ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡
2. የአሁኑ ግብርና ሚኒስቴር እንደ ተቋም የተመሰረተው በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት የእርሻና የመሥሪያ ቤት ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ በ1900 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም ግብርና እንደ ተቋም ከተቋቋመ ከአንድ መቶ አመታት በላይ ያስቆጠረ መሆኑን ያሳያል፡፡ በ1983 ዓ.ም የግብርናና የአካባቢ ጥበቃ ልማት ሚኒስቴር ተብሎ በአዲስ ድርጅታዊ መዋቅር ስራውን የጀመረ ሲሆን የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ያስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/1987 እንደገና ተቋቋመ፤ በጥቅምት 1994 ዓ.ም የኢፌድሪ መንግስት የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻልና ለማጠናከር በወጣው አዋጅ ቁጥር 256/1994 የግብርና ሚኒስቴር ተብሎ የተሰየመ ሲሆን ተጠሪነቱም ለገጠር ልማት ሚኒስቴር እንዲሆን ተወሰነ፤ በመቀጠልም መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት በመስጠት በ1996 ዓ.ም አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 380/1996 መሰረት የስራ ድግግሞሽን ለማስወገድና የተሻለ ስራ ለማከናወን ይቻል ዘንድ የግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ተዋህደው በአዲስ መልክ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲዋቀሩና እንዲደራጁ ተደርገ፤ ይህ ተቋም በ2002 ዓ.ም እንደገና ስያሜውን የግብርና ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ በመቀየር እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ከቆየ በኋላ በ916/2008 አስፈፃሚ አካላትን ለማደራጀትና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ መሰረት የእርሻና የተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር እና የእንስሳትና አሣ ሃብት ሚኒስቴር በሚል ለሁለት ተከፊሎ ሲሰራ ከቆየ በኃላ በ2010 ዓ.ም ስያሜውን በመቀየር የግብርናና እንስሳ ሃብት ሚኒስቴር በመባል የተደራጀ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት የግብርና ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ እየሰራ ይገኛል፡፡
3. የግብርና ሚኒስቴር በሴክተር መ/ቤት የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካትና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዋናነት

የግብርና ሴክተር ፓሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን የማስፈፀም፣ ክልሎችን የመደገፍና የማስተባበር ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

4. የእፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት በሶስት ቡድኖች ማለትም የፍቶሳኒተሬ አገልግሎት፣ የፀረ ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር ብድን እና የሰብል ምረት ጥራት ቁጥጥር የብቃት ማረጋገጫ ብድን በሚል ተከፍሎ እየሰራ ይገኛል፡፡
5. የእፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእፅዋት ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፣ የሀገሪቱን የግብርና ሀብት ጤናና ጥራት በመጠበቅ እንዲሁም በእፀዋት ተባይና በሽታ ምክንያት የሚከሰተውን የዜጎች ጤና ስጋት በመቀነስ የዓለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ፣ ከሀገር የሚወጡና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የግብርና ምርቶችና ውጤቶችን ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ የደንበኞችን ፍላጎት ማርካት፣ አደገኛ መጤ የነፍሳት ተባይ፣ መጤ አረም፣ ድንበር ዘለል በሽታዎችን፣ ነፍሳት እና ተባዮችን በመገደብና በመቆጣጠር የግብርና ተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ የእፅዋት ጤናና ጥራትን በመቆጣጠር፣ የበሽታና ተባይ ቅኝት በማካሄድ፣ የግብዓት ጥራት ቁጥጥር አገልግሎትን አሰራር በማቀላጠፍና ሽፋኑን በማሳደግ የእፅዋትና እፅዋት ውጤቶችን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማሳደግ ራዕይና ዓላማ ይዞ የተዋቀረ ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይ

6. በ2017 የተፈጥሮ ሀብት መሰረቱ የተጠበቀ ዘመናዊ እርሻና ከድህነት የተላቀቀ ህብረተሰብ መፍጠር፣

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተልዕኮ

7. ህብረተሰቡን ከድህነት ለማላቀቅ፣ የላቀ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የዘርፉን እምቅ ሃብትና አቅም የሚጠቀምና ከፍተኛ ምርታማነትን ደረጃ የደረሰ፣ ለሀገር ሃብት ክምችት፣ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ መሰረት ለመጣል የሚያስችልና የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን የሚቋቋም ዘመናዊ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ስርዓት መዘርጋት፤ ለዚህም ተፈፃሚነት በገበያ የሚመራ ዘመናዊ የእርሻ ዘዴዎችን ማስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሃብትን መንከባከብ፣ ማልማትና ጥቅም ላይ ማዋል፣ የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የባለሀብትን ተሳትፎ ማሳደግ እና ሴቶችና ወጣቶችን ለልማት ማብቃትና ተጠቃሚ ማድረግ ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ

8. የግብርና ሚኒስቴር የተቋቋመበት ዋና ዋና ዓላማዎች፣

- ✓ የግብርናን አመራረት ወደ ገበያ ተኮር ያመራረት ስርዓት ማሸጋገርና የአርሶ አደሩን፣ የአርብቶ አደሩንና የከፊል አርብቶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋጽኦ ማድረግ፤
- ✓ ስር የሰደደ የምግብ እጥረት ተጋላጭ ለሆነው የህብረተሰብ ክፍል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፤
- ✓ የተፈጥሮ ሀብታችንን በመንከባከብና በአግባብ በመጠቀም ለግብርና ልማታችን የሚኖረውን አስተዋጽኦ ማሳደግ፤

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተለያዩ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም፡-

- ✓ የሰብል ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል ለአርሶ አደሩ፣ ለአርብቶ አደሩ፣ ለግል ባለሀብቱ እና በከተማ የእርሻ ስራ ላይ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡ የኤክስቴንሽንና የስልጠና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደረጋል፤
- ✓ ለገበያ የሚቀርብ የሰብል ምርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- ✓ ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከሀገር በሚወጡት እፅዋትና አዝርዕት ላይ የኳራንቲን ቁጥጥር ያደረጋል፤
- ✓ የእፅዋት በሽታዎች ወረርሽኝና ተዛማጅ ተባዮችን ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂነት እንዲለማና እንዲጠበቅ፣ የጥምር እርሻ ቴክኖሎጂ እንዲስፋፋ ያደረጋል፤
- ✓ የሰብል ምርት ግብአቶች አቅርቦት፣ ስርጭትና ግብአት አቅምን በመገንባት አስተማማኝ አቅርቦትን ያረጋግጣል፣ የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- ✓ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳዳርና ቁጥጥር ስራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤

- ✓ የሰብል ምርታማነትና ጥራትን የሚያረጋግጡ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን እንዲስፋፋ ያደረጋል፣ በአገር ውስጥ የሚባዙበትን ሁኔታም ያመቻቻል፤
- ✓ የሆርቲካልቸር ልማትን ያስፋፋል፤
- ✓ የቡና እና የሻይ ልማት እና ግብዓት የሚመለከቱ ስራዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤
- ✓ የህብረት ስራ ማህበራት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
- ✓ የአፈር ለምነት የሚሻሻልበትን፣ የአፈር ጤና የሚጠበቅበትን እና አገራዊ የአፈር መረጃ ስርዓት የሚዘረጋበትን ስልት ይነደፋል፤
- ✓ የገጠር ፋይናንስ ስርዓት እንዲዘረጋ እና ለአርሶ አደሮቹ አገልግሎቱ ተደራሽ እንዲሆን ያመቻቻል፤
- ✓ በሰብል ምርት ምርምር ባለድርሻ አካላት በቅንጅትና በትብብር የሚሰሩበትን ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ ለግብርና ልማት አጋዥ የሆኑ የአነስተኛ መስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደረጋል፤
- ✓ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት መዘረጋቱን ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ አገራዊ መረጃ ያደራጃል፤
- ✓ የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከሎችን ያቋቁማል፣ ይመራል፤
- ✓ የግብርና ምርምር እና የግብርና ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ስራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤
- ✓ የምግብ ዋስትና እና የገጠር የስራ እድል ፈጠራን የሚመለከቱ ተግባራትን ያስተባብራል፤

የሚሉት ናቸው፡፡

## <u>የዕፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት</u>

- ✓ በስራ ሂደቱ በየበጀት አመቱ የሚዘጋጁ የስራ እቅዶች ከተቋሙ ስትራቴጂያዊ ግቦች ጋር ተመጋጋቢነት ኖሯቸው እንዲዘጋጁና በተገቢው በጀት እንዲደገፉ የአፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ እንዲዘጋጁ በበላይነት ያስተባብራል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
- ✓ በስራ ሂደቱ የለውጥ ሰራዊት ኃይሎችን ለማፍራት በሚደረገው ጥረት አረአያ በመሆን ለተሻለ የስራ ውጤት የሚያነሳሳ የስራ አካባቢን ያመቻቻል፤

- ✓ የዳይሬክቶሬቱን ግቦች ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራትን በላቀ ደረጃ የሚደገፉ አሰራሮችን በማምጣት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
- ✓ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት የስራ ሂደቶች ቅንጅትና ትስስር ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ በስራ ሂደቶች መካከል የተጠናከረና ተመጋጋቢነት ያለው የስራ ግንኙነት እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል ይከታተላል፤
- ✓ በአለም አቀፍ ገበያ እውቅና ያለው የገበያ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ተወዳዳሪና ጥራቱን የጠበቀ የእፅዋት ምርት በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን ለማግኘት የWTO መስፈርት የሆኑትን (የSPS) ስምምነቶች ታሳቢ ያደረገ የቁጥጥር ስራ ይዘረጋል፤
- ✓ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና ወደ ውጭ የሚላኩ ዕፅዋትና ውጤቶቻቸው ከባዕድ ተባይ ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርአት ይዘረጋል፤
- ✓ የስጋት ትንተና ቅኝት ስራን በተደራጀ መልኩ ለመስራት የሚያስችል ስርአት ይዘረጋል፤
- ✓ ዳይሬክቶሬቱ ሀገራችን እያስመዘገበች ያለችውን እድገትና ወደፊት ልንደርስበት ከምናልመው የዕድገት ግብ ባገናዘበ መልኩ ቀድሞ ሲሰራባቸው ከነበሩ የኳራንቲን ጣቢያዎች በተጨማሪ አዳዲስ ጣቢያዎችን እንዲከፈቱ በማድረግ በተሸለ የሰው ሀይል ስራን አደራጅቶ ለመስራት ያለመ ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ የተደራጀ ዶመስቲክ ኳራንቲን እንዲተገበር ከክልሎች ጋር በጋራ በመሆን ስርአት ይዘረጋል፤
- ✓ የአገራችን ምርቶች በዓለም ገበያ ተቀባይነታቸው እንዲጨምር የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ ባዕድ የሆኑ የዕፅዋት ነፍሳት ተባዮች በሽታዎችና አደገኛ አረሞች ወደ አገራችን ገብተው የዕፅዋት ሃብታችንን እንዳይጎዱብን ከሚደረገው ጥንቃቄና የቁጥጥር ተግባር አንፃር የተሸለ ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ የአገሪቱን ግብርናና አካባቢ ከውጭ በሚገቡ መጤ ተባይ/በሽታ ወይም ተዛማጅ ዕፅዋት እንዳይጠቁ ለመከላከል የስጋት ትንተና ስራ በተደራጀ መልኩ እንዲሰራ የተሸለ ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ የከፍተኛና መካከለኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ሆነው ነገር ግን መግባታቸው ከኢኮኖሚ ጠቀሜታ ምዘና አንፃር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ እፅዋቱ ላይ ድህረ ኳራንቲን ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ያመቻቻል ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ በሀገራችን ጥራቱ የተጠበቀ ከፍተኛ ምርት ለማምረትና ለሰው፣ ለእንስሳትና ለአካባቢ ጎጂነታቸው ዝቅተኛ የሆነ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለተጠቃሚው በግብዓትነት እንዲውሉ ለማድረግ የመመዝገብ፣ የመፍቀድና የመቆጣጠር ስርዓት በተደራጀ መልኩ እንዲሰራ ስርዓት ይዘረጋል፤
- ✓ በአዋጅና በደንብ ላይ በተቀመጡ የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ለሚያስፈልጋቸው የግብርና ምርቶች መስፈርቶችና አሰራሮች ላይ በመመስረት ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ የአሰራር ስርዓቱን ይቆጣጠራል፤

- ✓ በሥራ ሂደት ተግባራት ወቅት የሚከሰቱ ችግሮችን በውይይት ይፈታል፣ የበላይ አመራር ውሳኔን የሚፈልጉ ጉዳዮችን በወቅቱ ለዘርፉ ያቀርባል፣ በሚሰጠው ምላሽ መሰረትም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- ✓ ለደንበኞች ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የሥራ ሂደቱን ለመቅረፅና ለማሻሻል የሚከናወኑ ተግባራትን በበላይነት ያስተባብራል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤
- ✓ የሥራ ሂደቱን በተመለከተ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር በሚካሄዱ የተለያዩ ስብሰባዎች፣ የምክክር መድረኮች ላይ ይሳተፋል፣ ወቅታዊ አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰጣል፤
- ✓ የውጤት ተኮር ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ የክትትል ስርዓት በማዘጋጀት የስራ ሂደቱ የደረሰበትን የአፈፃፀም ደረጃ ይገመግማል፣ የግምገማውን ውጤት በስሩ ለሚገኙ የስራ ሂደቱ ሰራተኞች ያሳውቃል፣ አፈፃፀሙን የሚያሻሽልበትን አስፈላጊ እርምጃ ይወስዳል፤
- ✓ በስራ ሂደቱ የላቀ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ባለሙያዎች /ቡድኖች አስፈላጊውን ማትጊያ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ ሌሎች ባለሙያዎችንም ለተሻለ ውጤት ለማብቃት ምክርና ትምህርት ይሰጣል፣ በተደጋጋሚ የስራ ብቃት የሚያሳዩ ባለሙያዎችን ለዘርፉ ያሳውቃል፣ ውሳኔ እንዲሰጥበትም ይከታተላል፤

በተጨማሪም የዳይሬክቶሬቱን ግቦች ሊያሳኩ የሚችሉ ተዛማጅና ተደጋጋፊ የሆኑ ከዳይሬክተር ጀነራሉ የሚሰጡ ተግባራት ሁሉ ያከናውናል፤

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአሁኑ ጊዜ በአንድ ሚኒስትር እና በአራት ሚኒስትር ዴኤታዎች የሚመራ ሲሆን የእርሻ ልማት ዘርፍ፣ የእንስሳት ሀብት ዘርፍ፣ የተፈጥሮ ሀብትና ምግብ ዋስትና ዘርፍ እና የግብርና ግብዓት ግብይት ዘርፍ ሲኖሩት እነዚህም በሚኒስትር ዴታዎች የሚመሩ ናቸው፡፡ በአራት ዘርፎች ስርም 32 ዳይሬክቶሬቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህ በተጨማሪ ለሚኒስትሩ ተጠሪ የሆኑ ሌሎች 16 ዳይሬክቶሬቶች አሉት፡፡ **/የሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅር በአባሪ 1 ተያይዟል/**

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሰው ኃይል

11. በሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅር /መደብ/ መሰረት የተፈቀደው የሰው ኃይል ብዛት 2,122 ሲሆን በሰው ኃይል የተሞላው 807 ወንዶችና 475 ሴቶች በድምሩ 1,282 ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 840 ክፍት መደብ አለ፣ በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመዋቅሩ ከተፈቀደለት የሰው ኃይል ያሟላው 60.41% ነው፡፡ በኦዲቱ አፈፃፀሙ የሚታየው የዕፅዋት ጤናና ምርት

ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለፀረ ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር ኬዝ ቲም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ በመዋቅሩ የተፈቀደው የሰው ኃይል 35 ሲሆን ስራ ላይ ያለ ወንድ 12፣ ሴት 3 ድምር 15 ከዚህ ውስጥ 20 ክፍት መደብ ያለው መሆኑና ከተፈቀደለት የሰው ኃይል ያሚላው በመቶኛ 42.85% ብቻ ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

12. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2008-2010 ዓ.ም ድረስ የተመደበለት በጀትና ስራ ላይ የዋለው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| የበጀት ዓመት | | የተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2008 | መደበኛ | 260,797,000.00 | 132,380,521.04 | 50.75% |
| | ካፒታል | 614,777,950.00 | 21,760,160.13 | 3.54% |
| 2009 | መደበኛ | 142,488,425.00 | 138,767,119.19 | 97.38% |
| | ካፒታል | 490,835,430.00 | 136,076,409.75 | 27.72% |
| 2010 | መደበኛ | 273,318,900.55 | 167,530,153.92 | 61.29% |
| | ካፒታል | 51,655,124.00 | 4,380,247.36 | 8.48% |

## የኦዲቱ ዓላማ

13. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን መገምገም ሲሆን፣ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘም የአሰራር ችግሮችን ለይቶ በማውጣት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

14.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደር እና ቁጥጥር ስርዓት መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

15.ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ለማሳካት የሚያስችሉ አራት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፡-

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አመዘጋገብ፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አጠባበቅ እና አወጋገድ ስርዓቱ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና የኳራንቲን ጣቢያዎችን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የተከሰቱ ችግሮችን በመለየት አስፈላጊውን ግብረ መልስ እየሰጠ ስለመሆኑ መገምገም፣
4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና ኳራንቲን ጣቢያዎችን እንዲሁም በዘርፉ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትን በመለየት በቅንጅት እየሰራ መሆኑን መገምገም፣ የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

16.በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ አራት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 27 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ 916/2008 እና የፀረ ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ 674/2002፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ እስትራቴጂክ እና አመታዊ ዕቅዶች፣ የፀረ ተባይ መሳሪያዎች አጠቃቀም ባለሙያ የስራ ዝርዝር መግለጫ፣ የዕፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ዕቅድ ክንውኖች እና የተለያዩ የጽሑፍ ሰነዶች፣ ደብዳቤዎች፣ መልካም ተሞክሮዎች፣ የባለድርሻ አካላት ወርኃዊ ሪፖርቶች፣ የመስክ ምልከታዎች እና ቃለ መጠይቆች ናቸው፡፡ በተዘጋጁት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ

መስፈርቶች ላይም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ተደርጎ ተቀባይነትን አገኝቷል፡፡

## የኦዲት ወሰንና ዘዴ

17. ኦዲቱ የተከናወነው ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት ሲሆን የኦዲት ሪፖርቱ የሸፈነው ሦስት የበጀት ዓመታትን (ከ2008 — 2010) ዓ.ም ድረስ ያለውን የስራ አፈፃፀም ነው፡፡

18. በኦዲቱ ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በተጨማሪ በናሙና በተመረጡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ የሲዳማ ዞን፣ የወንዶ ገነትና የሀዋሳ ዙሪያ ወረዳዎች፣ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የምስራቅ ሸዋና የምዕራብ አርሲ ዞን፣ የሻሸመኔ፣ የዱግዳና የአዳሚ ቱሉ ጂዱ ኮምቦልቻ ወረዳዎች፣ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የባህርዳር ዙሪያ ወረዳ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን፣ የጎዛምን ወረዳ፣ የደቡብ ጎንደርና የማዕከላዊ ጎንደር ዞን፣ የጎንደር ከተማ አስተዳደር፣ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ምዕራብ ዞንና የሁመራ ቃፍታ ወረዳ፣ የዝዋይ ሮዝና የኤኪው ሮዝ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅት፣ የአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማምረቻ ፋብሪካ፣ የይሳከር የግብርና ግብዓት አስመጭ ኃ/የተ/የግ/ድርጅት፣ የግሪን ማርክ ኸርቨስ ኃ/ የተ/የግል ማህበር፣ የቦሌ ካርጎ፣ ሁመራ፣ መተማ፣ የሞጆ ደረቅ ወደብ፣ የአዳማ እፅዋት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ የባህርዳር የእፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ባለስልጣን፣ የደብረ ማርቆስ የእፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ የጎንደር የእፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በዩኒየኖችና በማህበራት፣ የፀረ ተባይ ኬሚካል በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላትን እንዲሁም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የተገኙ ከፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓት ጋር የተያያዙ ዶክመንቶች በመከለስ፣ በአካል በመስክ በመገኘት፣ የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እንዲሁም ቼክ ሊስት በማስሞላት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ (**ዝርዝሩ በአባሪ ሶስት ተያይዟል፡፡**)

# የዕፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የሥራ ፍሰት መግለጫ (System Description)

- ፀረ ተባይ ኬሚካሉ ለምዝገባ ብቁ መሆኑን ማለትም በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያስከትልና ለታለመለት አላማ ብቁ ሆኖ በገምጋሚው ከተገኘ የዶዜር የቴክኒክ ግምገማ ውጤት ባጭሩ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ለውሳኔ ይቀርባል፡፡
- ተገምግመው የፀደቁ ግብአቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለግብአቶች የምዝገባ ሰርተፊኬት መስጠት፤ በድረ ገፅ ማሰራጨትና በአመቱ የተመዘገቡ ግብአቶችን ዝርዝር በህትመት በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማሳወቅ ስራ ይከናወናል፤ አንድ ጊዜ የተመዘገበ ፀረ ተባይ የአገልግሎት ዘመኑ ለአምስት ዓመት ሲሆን ለተጨማሪ አምስት አመት አገልግሎት እንዲሰጥ ሲቀርብ ሙከራ ማካሄድ ሳያስፈልግ በድጋሚ ተመዝግቦ በግብአትነት ይቆያል፡፡
- በየደረጃው የሚገኙ መረጃዎችን፣ ጥቆማዎችንና አስተያየቶችን በየደረጃው ያሉ ሰራተኞች በማጠናቀር ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፣ ማስተካከያ ርምጃ መውሰድና ወደ መረጃ ቋት መላክ ይጠበቃል፡፡
- የተመዘገቡና የማስገቢያ ፈቃድ የተሰጣቸውን ፀረ ተባዮች በመግቢያ በሮች ላይ ትክክለኛ መለያ እንደተለጠፈባቸውና እንደዚሁም ስለትክክለኛነታቸው ምርመራ ይደረጋል፡፡
- ፀረ ተባይ ምዝገባና ቁጥጥርን በተመለከተ መረጃዎችን ለዚሁ ተግባር በተዘጋጁ የዳታ ቤዝ ፕሮግራሞች (የፀረ ተባይ ክምችትና የተመዘገቡ ፀረ ተባዮች መረጃ (PSMS) የፀረ ተባይ ምዝገባ አስተዳደር ሲስተም (PREMAS) አማካኝነት ይይዛል)፣ የተመዘገቡ ፀረ ተባዮችን በድረ ገፅ በመመዝገብ ያሥገባል፡፡
- ፀረ ተባይ ለማስመዝብ የሚቀርቡ የፀረ ተባይ ዶዜዎች የቀበላል፣ አስፈላጊ ሰነዶች መያዛቸውን ያጣራል ዶዜው ሲሟላ ለተገቢው ባለሙያ ለግምገማ ያስተላልፋል፤ የፀረ ተባይ ዶዜዎች ውስጥ ተገቢው ጥናቶችና ዳታዎች መያዛቸውን ይመረምራል፣ ሲሟላ የቴክኒክ ግምገማ ያካሂዳል፡፡
- የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርአት ፀረ ተባይ ከውጭ አገር በማስገባትና በማከፋፈል፣ የማጠን ስራ በማካሄድ፣

# ክፍል ሁለት
# የኦዲት ግኝቶች

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የሚመለከቱ ህጎች ማዘጋጀቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ

19. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን ለመተግበር የሚያስችለው ደንብ፣ መመሪያ እና እስታንዳርድ ሊያዘጋጅና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
20. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 674/2002 የወጣ ቢሆንም ዝርዝር ጉዳዮችን መሰረት ያደረገ ስራዎችን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊያሰራ የሚያስችል በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የወጣና ወደ ታች የወረደ ደንብ፣ መመሪያና እስታንዳርድ የሌለና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ እንዲሁም የፀረ ተባይ ኬሚካሎችን አፈፃፀም በተገቢው ሁኔታ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡
21. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡- የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደር እና ቁጥጥር በተመለከተ አዋጅ ያለ ሲሆን ስራውን ሊያሰሩ የሚያስችሉ ደንብ፣ መመሪያና እስታንዳርድ አለመዘጋጀቱ፣ እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ደንቦች እንዲወጡ ለበላይ አመራሩ ጥያቄ ቢቀርብም ቶሎ ምላሽ እንደማይሰጥ ገልፀዋል፡፡
22. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ እንደ ሚኒስቴር መ/ቤት የአቅምና የክህሎት ክፍተት ችግር እንዲሁም የሰው ሃይል እጥረት በመኖሩ እስካሁን የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደር እና ቁጥጥር ደንብ፣ መመሪያና እስታንዳርድ ሊወጣ አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

23.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ የወጡ ህጎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንብ፣ መመሪያ እና እስታንዳርድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ባለማድረጉ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደር እና ቁጥጥር ስራው በብቃት፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ እንዳይቻል አንዱ ምክንያት ሆኗል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በላብራቶሪ መርምሮ መመዝገቡን በተመለከተ

24.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም በወጣው መሰረት ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነቱንና ጥራቱን በላብራቶሪ መርምሮና አረጋግጦ ሊመዘግብ ይገባል፡፡

25.የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡- በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነታቸውና ጥራታቸው በላብራቶሪ ተመርምሮና ተረጋግጦ እንደማይመዘገብና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአሁኑ ሰዓት እየተመዘገቡ ያሉት እንዲሁ ዶክመንት /ወረቀት/ በማየት ብቻ መሆኑንና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተገቢው ሁኔታ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት እንደሌለና ተግባራዊ እንዳላደረገ ገልፀዋል፡፡

26.እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ ፋብሪካዎች /ድርጅቶች/ ጥራቱን የጠበቀ ምርትና ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ወደ ውጭ ሀገራት ለመላክ፣ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሃገር ውስጥ ለማምረት እና ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው፣ የተደራጀና ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ ላብራቶሪ አገልግሎት የሌላቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

27.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ፍቱንነት በምርምር ተቋማት በላብራቶሪ ወይም በመስክ ላይ ከታየ በኃላ እንደሚመዘገብ እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ላብራቶሪ ትልቅ ጥናት፣ እራሱን የቻለ የግንባታ ቦታ፣ በጀት እና በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል ባለመኖሩ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ጥራቱንና ደህንነቱን የጠበቀ አለም

አቀፍ ላብራቶሪ ለመገንባት አለመቻሉን፣ በዚህም የፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ጥራታቸውንና ደህንነታቸውን በማወቅና በመለየት በኩል በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተሰራበት እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡

28.በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም ፀረ ተባይ ኬሚካል በላብራቶሪ መርምሮና አረጋግጦ ባለመመዝገቡ፣ ህብረተሰቡ ደህንነታቸውንና ጥራታቸውን ያልተረጋገጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን እየያዛቸውና እየተጠቀመባቸው በመሆኑ በሰው፣ በእንስሳት፣ በአካባቢ እና በዕፅዋት ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

## <u>ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ቅሪት መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ መኖሩን በተመለከተ</u>

29.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በግብርና ምርቶች ላይ ሊኖር የሚችል የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

30.በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው በሀገሪቱ ውስጥ በግብርና ምርቶች ላይ ሊኖር የሚችል የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ እንደሌለና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህ አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ እንዲኖር ስለሰራው ስራ ማስረጃው ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡

31.የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ቅሪትና ጥራት ለመቆጣጠር የሚያስችል የተጠናከረና ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው የጥራትና ቁጥጥር ላብራቶሪ አለመኖሩ፤
- ✓ የዕፅዋት ኳራንቲን ጣቢያዎች በላብራቶሪ የተሟሉ አለመሆንና አለም አቀፍ እስታንዳርድን በሚጠይቀው መሰረት ተሟልተው አለመገኘታቸው፤

- ✓ ከጎረቤት ሀገራት በኮንትሮባንድ የሚገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ያልተመዘገቡ እና ጥራታቸው በላብራቶሪ ያልተረጋገጠ በመሆኑ፤ እንዲሁም በኤክስፓርት ሰብሎች ላይ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ቅሪት በመገኘቱ በኤክስፓርቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፤
- ✓ ወደ ውጪ በሚላኩ የግብርና ምርቶች ላይ በተገኘ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ቅሪት ምክንያት በከፍተኛ ወጪ የተመረተ ምርት እንዲወገድ መደረጉ፣ ተቀባይነቱና ተፈላጊነቱ እየቀነሰ መምጣቱ፣ ለማሳያ፡- ወደ ጃፓን በተላከ የቡና ምርት ላይ የኦርጋኖ ክሎሪን ዝርያ ያላቸው ፀረ ተባይ ቅሪት መገኘቱ፣ እ.ኤ.አ አቆጣጠር ከ2014-2016 በተከታታይ ወደ ጣሊያን ለምግብነት እንዲውሉ የተላኩ ምርቶች በፀረ ተባይ ቅሪት ምክንያት ከድንበር ላይ እንዲመለሱ መደረጉ፣ ወደ አውሮፓ በተላከ ነጭና ቀይ ቦለቄ ውስጥ ለግብርና እና ለወባ ትንኝ ማጥፊያ የሚውሉ የፀረ ተባይ ቅሪት በመገኘቱ በምርቱ ጥራት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደሩ ለመግዛት እንደተቸገሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

32.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የባለሙያ የአቅም ክፍተት፣ በሙያው የሰለጠነ የሰው ሀይል ስለሌለ እና ያሉትም ባለሙያዎች በተለያየ ጊዜ የሚለቁበት ሁኔታ በመኖሩ እንዲሁም የፀረ ተባይ ቅሪት መለየት የሚያስችል ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ ባለመገንባቱ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡና በሚመረቱ የግብርና ምርቶች ላይ የፀረ-ተባይ ቅሪት መለየት አለመቻሉን እንዲሁም የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ይዘት፣ ጥራትና እውቅና ያለው ላብራቶሪ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

33.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ ባለመኖሩና ተግባራዊ ባለማድረጉ በሀገሪቱ ውስጥ በሚመረቱ እና ወደ ውጭ ሀገራት በሚላኩ የኤክስፓርት የግብርና ምርት ውጤቶች ላይ የፀረ ተባይ ኬሚካል ቅሪት እንዲኖር እና ሀገሪቱ በከፍተኛ ወጪ የምታመርታቸው ምርቶች እንዲወገዱ፣ የውጭ ሀገራት ተቀባይነትና ተፈላጊነቱ እየቀነሰ እንዲመጣ እንዲሁም በኤክስፓርቱ ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድር አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማስታወቂያዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ሳይመዘገቡ እና ፍቃድ ሳያገኙ እንዳያስተዋውቁ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ፣ ምንጫቸው ያልታወቁና በህገወጥ በኮንትሮባንድ የገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ከሱዳን በመተማና ሁመራ፣ ከጅቡቲና ከሱማሊያ በድሬደዋና ሀረር፣ ከኬንያ በሞያሌ የሚገቡና እና በሀገሪቱ የተለያዩ የገበያ ቦታዎች፣ የመንገድ ዳሮች የፀረ-ተባይ ኬሚካል ፓስተሮችን የሚለጥፉበት፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ካላንደሮች እና ቡክሌቶች የሚሰራጩበትና የሚበተኑበት እንዲሁም በጠርሙስ አሽገው በመኪና በመዘዋወር የትንኝ፣ የአይጥ፣ የቁንጫ፣ የትኋን እና የበረሮ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ናቸው በሚል በማይክራፎን የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በሰፊው የሚያስተዋውቁበት ሁኔታ መኖሩ እና በዚህ ዙሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንደማይደረግ ታውቋል፡፡

36. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

- ✓ የዘራ ኢንጂነሪንግና ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር በንግድ ስሙ Zera Mouse Killer ፀረ ተባይ ኬሚካል ምዝገባው ሳይጠናቀቅ ፀረ ተባይ ኬሚካሉን ከ15/05/2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 17/08/2010 ዓ.ም በማምረት ለገበያ እያቀረበ እንደነበረ፣ የፀረ ተባይ ኬሚካል ምርቱ የራሱ በሆነ በተዘጋጀለት የመሸጫ ቦታ ብቻ ለሽያጭ ማቅረብ ሲገባ ነገር ግን ምርቱን በመንገድ ዳሮች፣ በከተማው ውስጥ በተለያዩ ሱፐርማርኬቶች እና በፀረ ተባይ መሸጫ መደብሮች ውስጥ በህገወጥ መንገድ እየተሸጠ እና በአየር ላይ በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ማስታወቂያውን የሚያስተላልፍበት ሁኔታ መኖሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

37. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር መዋቅሩ ከፌደራል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ሰንሰለቱን ጠብቆ የወረደ ባለመሆኑ፣ የሰው ኃይል እና የግብዓት ችግር በመኖሩ እንዲሁም ለዘርፉ ግንዛቤና ትኩረት ባለመሰጠቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ሳይመዘገቡና ፍቃድ ሳያገኙ ሲያስተዋውቁ ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉ ገልፀዋል፡፡

38. በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የፀረ-ተባይ ማስታወቂያዎች ሳይመዘገቡና ፍቃድ ሳያገኙ እንዳያስተዋውቁ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ ምንነታቸው ያልታወቁ /ያልተረጋገጡ/ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በማስተዋወቅ እና በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ምንጫቸው ያልታወቁ፣ የተመረቱበት ቀን፣ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው እና መለያቸው የማይታወቅ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንዲሸጡ በማድረግ በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋት እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ /ችግር/ ከመፍጠራቸውም በላይ እስካሁን ስላደረሱት እና እያደረሱ ስላለው የጉዳት መጠን እና ምንነት እንዳይታወቅ አድርጓል፡፡

## <u>ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥን በተመለከተ</u>

39. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

40. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት የሚከተሉት ታይተዋል፡-

**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓትን በሚመለከት፡-**

- ✓ **ቲ ኤም አግሮ ኢንዳስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**፣ የኬሚካልና የዘር አስመጭነት ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ቢሆንም በድርጅቱ የተቀጠረው ባለሙያ በሌላ መንግስታዊ መ/ቤት እየሰራ ያለ መሆኑ፣ የተመዘገበ ፀረ ተባይ ኬሚካል ሳይኖረው ቢሮ ውስጥ

የኬሚካል ሳምፕሎች መገኘታቸው፣ መጋዝኑን እንዲያሳይ ሲጠየቅ መጋዝኑን ለማሳየት ፍቃደኛ አለመሆኑ፣ የፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝኑን አድራሻ ሲጠየቅ የተለያየ የመጋዝን አድራሻ መስጠቱ፣

- ✓ **አስቻለው ሙላቱ አስመጪና ላኪ፣** ድርጅቱ መጋዘኑን ከፍቶ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፣ ፍቃድ ካወጣ ስድስት ወር ቢሆነውም መጋዘኑ ውስጥ ምን እንዳለ አለመታወቁ፣
- ✓ **ዓብዱላሂ ሽፋ፤** በ2007 ዓ.ም መስከረም ወር ብቃት የወሰደ ቢሆንም ፀረ ተባይ ሳያስመዘግብ ፀረ ተባይ እያመረተ እንደሚሸጥ ማረጋገጥ መቻሉ፣ ፋብሪካው ከአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አንፃር ሲታይ ወንዝ ዳር አካባቢ መሆኑ፣ ፍብሪካው የማምረቻ ፋሲሊቲው የተሟላ አለመሆኑና ተዛማጅነት የሌለው የሳሙና ማምረቻ ማሽን መገኘቱ፣ በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፋብሪካዎች/ድርጅቶች/ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፈቃድ ወጥ መመሪያ በሌለበት ሁኔታ የተሰጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. እንዲሁም ያልተመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እና ሌሎች የእርሻ ኬሚካሎች ከውጪ ለማስመጣትና ለመጠቀም ወይም ለመሸጥ የሚፈቀድላቸውን /የተፈቀደላቸውን/ ድርጅቶች የተፈቀደና የለማ የእርሻ መጠን ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ወቅታዊ መረጃ በመጠየቅ መዝግቦ በመያዝ የሚያስፈልጋቸውን የእያንዳንዱን ኬሚካል አመታዊ ፍጆታና የአጠቃቀም መጠን /Rate of application/ እና የድግግሞሽ /Frequency/ ታሳቢ በማድረግ ለእርሻቸው አገልግሎት ብቻ የሚውል ኬሚካል ማስገቢያ ፈቃድ እንዲሰጣቸው አለመደረጉ፣

42. በተጨማሪም ዘራ ኢንጂነሪንግና ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር የፀረ ተባይ ኬሚካል ምርቶችን ለማምረት የንግድ ፍቃድ በንግድ ሚኒስቴር መሰጠት ያለበት ቢሆንም የንግድ ስራ ፍቃድ በ15/05/2007 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ፀረ ተባይ እና ሌሎች የግብርና ኬሚካሎች መፈብረክ /ማምረት/ በሚል ፈቃድ መሰጠቱ እና አምራች ድርጅቱ ፍቃድ በመሰጠቱ ብቻ በንግድ ስሙ Zera Mouse Killer /የአይጥ መርዝ/ ፀረ ተባይ ኬሚካል እስከ 17/08/2010 ዓ.ም ድረስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይመዘገብ የፀረ ተባይ ኬሚካሉን እያመረተ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ለህብረተሰቡና ለአርሶ አደሩ በገበያ ላይ እያስተዋወቀ እና እያሰራጨ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

43. በተመሳሳይም የማዕከላዊ ጎንደር እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት ለአዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ድርጅት ዩኒየኖች ማለትም ደባርቅ ማህበር፣ መተማ ዩኒየን፣ ፀሀይ ዩኒየን፣ ሰላም ዩኒየን፣ ጉና ዩኒየን፣ መገናኛ ዩኒየን፣ ራስ ጋይንት ዩኒየን፣ መረከብ ዩኒየን በግብርና መ/ቤት ሳይመዘገቡና ብቃት ሳይኖራቸው እንዲሁም የንግድ ፍቃድ ሳይሰጣቸው ፀረ ተባይ ኬሚካል እንዲያቀርቡ ደብዳቤ የሚፅፍበት ሁኔታ መኖሩ እና በዞኑ ያሉ ህብረት ስራ ዩኒየኖች የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ለአርሶ አደሩና ለህብረተሰቡ የሚያቀርቡበት፣ የሚሸጡበት እንዲሁም የሚያስራጩበት ሁኔታ መኖሩ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ ክልሉን /ዞኑን/ በተገቢው ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

44. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የባለሙያዎች የአቅም ክፍተት፣ የሰው ኃይል እጥረት እና ለዘርፉ ትኩረት ካለመስጠት አንፃር በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡

45. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተገቢው ሁኔታ ባለመስጠቱና ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ በሀገሪቱ ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይታወቁ፣ ያልተመዘገቡና ብቃት የሌላቸው ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካል አምራቾች፣ አከፋፋዮች እና ቸርቻሪዎች እንዲበራከቱ ምክንያት ሆኗል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ ያላቸው መሆናቸውን በተመለከተ

46. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ያላቸው እና ከተመረቱ 6 ወር ያላለፈባቸው ስለመሆኑ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

47. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሂዳቸው

የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡- በሞጆ ደረቅ ወደብ፣ በቦሌ ካርጎ ኳራንቲን ጣቢያ መግቢያ በሮች በኩል በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ከተመረቱ 6ወር ያለፋቸው እና አስፈላጊውን መስፍርት ሳያሟሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ መፈቀዱ **ለማሳያ፡-**

- ✓ በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማዘጋጃ አክስዮን ማህበር 96,000 ኪ/ግ ታዮኔክስ /ኢንዶሰልፋን/ 97% ቴክኒካል ፀረ ተባይ ኬሚካል ምርቱ እንዲገባ ከተፈቀደበት ጊዜ በ3 ወር ዘግይቶ፣ የተለያየ ማምረቻ መለያ ቁጥር ሳይሰጠው፣ የማራዘሚያ ፈቃድ ሳይወስድ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፍተሻ ሳይደረግለት በዲሴምበር 2015 ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ መደረጉ፣
- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካል የማስገቢያ ፍቃድ በኢንስፔክሽን ፎርም ላይ የተመረተበትን ቀን ሳይፃፍ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የተፈቀደበት ቀን ብቻ የሚፃፍ በመሆኑ መቼ እንደተመረተ የማይታወቅ እና ከተመረተ 6 ወር ያላለፈው ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ **ለምሳሌ Raji Agro-industry** በቀን 06/12/2017 በAuthorization No.21/126/01/384/2017 መሰጠቱ፤
- ✓ በመግቢያ ኳራንቲን ጣቢያዎች የኢንስፔክሽን ስራ በሚሰራበት ሰዓት አስፈላጊውን መስፍርት ሳያሟሉ ወደ ሀገር ውስጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን እንዳይገቡ ለማድረግ ሲሞከር በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል እንዲለቀቅ በቃል መመሪያ የሚሰጥ መሆኑ፤
- ✓ **ሼር ኢትዮጵያ ኃ.የተ.የግል ማህበር** ከተመረተ 6 ወር ያለፈው ቴፒኪ /Teppeki/ የተባለ ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ ማስገባቱ፤
- ✓ **ኒዶፒያ ኦርቲ አግሮ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግል ማህበር** Ortiva እና Folio Gold ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለያሲን ለገሰ ጆንሰን የአበባ እርሻ እና ዜድ ኬ ፍላወርስ ኃ.የተ.የግል ማህበር ከተመረቱ 6 ወር ያለፈባቸው ቢሆንም ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ፈቃድ የተሰጣቸው መደረጉ፤
- ✓ **መኩቡ ኢንተርፕራዝ ኃ.የተ.የግል ማህበር** Fastac R እና Stomp R የተባሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከተመረቱ 6 ወር ያለፈባቸው ቢሆንም ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉ፤

- ✓ ዜድ ኬ ፍላወርስ እና ያሲን ለገሰ ኃ/የተ/የግ/ማህበር **በኢዶፒያ ሆርቲ አግሮ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር** በኩል 240 ሊትር ሬጀንት /Regent/ የተባለ ፀረ ተባይ ኬሚካል ከተመረተ 6 ወር ያለፈው ቢሆንም ወደ ሀገር ውስጥ እንደገባ መደረጉን፤
- ✓ ማኮቦ ኢንተርፕራይዝ ፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጪ ድርጅት ከተመረተ 7 ወር የሆነው ፀረ ተባይ ኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከተመረቱ 6 ወር ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ጥቅም ላይ ይውላሉ በሚል ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ እንዳለ እና የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይመዘገቡ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ሳይኖራቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡

49. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለማከፋፈል ሳይሆን ለምርምር ወይም ለሙከራ ብቻ የሚውል መጠኑን በመወሰን እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ በአስገዳጅ ሁኔታዎች የሚፈቅድ ቢሆንም አስገዳጅ ሁኔታዎች አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብና መመሪያ የሚወሰኑ እንደሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም ክፍል ሁለት አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 4 እና ክፍል ሦስት አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 4 ቢገለፅም አዋጁ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ደንብና መመሪያ በሌለበት ለአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ እያስገቡ መሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተመረቱ 6 ወር ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ቢገቡ የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ጥቅም ላይ ይውላሉ በሚል ሲገቡ በሚኒስቴሩ የተፈቀደበት /የተወሰነበት/ ማስረጃ ለኦዲቱ ባለመቅረቡ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

50. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ የላቸው፣ ከተመረቱ 6 ወር ያላለፈባቸው ስለመሆናቸው በተገቢው ሁኔታ ባለማረጋገጡ እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር

ውስጥ ቢገቡ የአገልግሎት ጊዜያቸው ከማብቃቱ በፊት ጥቅም ላይ ይውላሉና ኢንቨስትመንትን ያስፋፋሉ በሚል ለአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች ምንም ዓይነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ሳይኖራቸውና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይመዘገቡ በልዩ ሁኔታ ወደ ሀገር ውስጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ማስገባታቸው የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳድር እና ቁጥጥር ስራው የላላና ለህገ ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስገቢዎች በር እንዲከፍት ከማድረጉም በተጨማሪ ለዘርፉ ስራ ብልሹ አሰራር እንዲፈጥር አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን ስራ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር መኖሩን እና በመዋቅሩ የተቀመጠውን የሰው ሃይል ማሟላቱን በተመለከተ

51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኘውን የአስተዳደር አካላት ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር ሊኖረው እና በመዋቅሩ የተቀመጠውን የሰው ሃይል በስብጥር መሰረት ሊያሟላ ይገባል፡፡

52. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሂዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው ሰፊና ሀገራዊ እንድምታው የገዘፈ ቢሆንም በዕፅዋት ጤናና ምርት ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ለፀረ ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር ኬዝ ቲም የተቀጠረው የሰራተኛ ቁጥር ከስራው ጋር አለመጣጣሙና መደቦች የተሟሉ አለመሆናቸው፣ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ በመዋቅሩ የተፈቀደው የሰው ኃይል 35 ሲሆን ስራ ላይ ያለ ወንድ 12፣ ሴት 3 ድምር 15 ከዚህ ውስጥ 20 ክፍት መደብ ያለው መሆኑና ከተፈቀደለት የሰው ኃይል ያሟላው በመቶኛ 42.85% ብቻ መሆኑ፣ በተፈቀደው መደብ ላይ የሰራተኞች ቅጥር አለመፈፀሙ፣ ያለው ሰራተኛ ሲለቅም በምትኩ ያለመቅጠር፣ የአስተዳደራዊ ስራዎች መዋቅራዊ ትስስር አለመኖሩ፤

- ✓ በናሙና በታዩ ክልሎች ያለው የፀረ ተባይ ኬሚካል የሰው ኃይል አወቃቀር የሰብል ጥበቃ ስራ መደብ ተመሳሳይ ባለመሆኑ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፣ ሥልጠናዎችን ለማዘጋጀት እንዲሁም ተባይ ሲከሰት የዘመቻ ስራ ከማድረግ በዘለለ ልምድ እና እውቀትን መሰረት ባደረገ መልኩ በሽታን እና ተባይን ለይቶ ትክክለኛውን ፀረ ተባይ ኬሚካል በተገቢው መጠን ተጠቅሞ የመከላከል እርምጃ ለመውሰድ የአቅም ውስንነት ያለ መሆኑ፤
- ✓ በመተማና በሁመራ የኳራንቲን ጣቢያዎች የፀረ ተባይ ኬሚካልን ስራ የሚሰራ ምንም ዓይነት ባለሙያ አለመኖሩና ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ በኳራንቲን ጣቢያዎቹ  የፀረ ተባይ ኬሚካል የቁጥጥር ስራ አለመሰራቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡

53. እንዲሁም በሞጆ ደረቅ ወደብ፣ በቦሌ ካርጎ እና በአዳማ እፅዋት ኳራንቲን ጣቢያ ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚያሰራ መዋቅርና የተሟላ የሰው ኃይል አለመኖሩ፣ እንዲሁም በኳራንቲን ጣቢያዎቹ የፀረ-ተባይ ኢንስፔክተር/ ተቆጣጣሪ/ እንደሌለና በተደራቢነት የእፅዋት ኳራንቲን ጣቢያ ኢንስፔክተሮች /ተቆጣጣሪዎች / ስራውን እንደሚሰሩት ይህም ያለ ኃላፊነታቸው እና ያለ ደብዳቤ እንዲሁም ያለ ውክልና ስራው እንደሚሰራ፣ በተጨማሪም ከ1991 ዓ.ም ጅምሮ ያለ ምንም ህጋዊ ደብዳቤ በኃላፊነት እየሰሩ መሆኑ፣ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ስራ በእፅዋት የስራ ሂደት ማህተምና ቲተር እንደሚሰራ፣ ነገር ግን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በህጋዊ መንገድ ተቀጥረው የሚሰሩ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ኢንስፔክተሮች መኖራቸውና የፀረ-ተባይ የፍቃድ አሰጣጥ ስራውን እየሰሩ መሆኑን በተጨማሪም ሰራተኛው በየዓመቱ በተለያየ ቦታ የሚሰራበትና የሚዘዋወርበት ሁኔታ መኖሩ ይህም መረጃዎች በተለያየ ሰው ስለሚመዘገቡ በግልፅ የማይገኙበት ሁኔታ መፈጠሩ፣ ሠራተኛው በሙያው በሰለጠነበትና በሚመጥነው ቦታ አለመመደቡ፣ በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

54. በተጨማሪም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የእፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ባለስልጣን መ/ቤቱ ቢቋቋምም ይህ ኳራንቲን ባለስልጣን ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ወጥ የሆነ አደረጃጀት የሌለው መሆኑ እና ዞን ላይ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተንጠልጥሎ ያለ ሲሆን ወረዳ ላይ በውክልና እንደሚሰራ መሆኑ፣ እንደ ዞን እራሱን ችሎ የተቋቋመ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ባለሙያ አለመኖሩና

የሰብል ጥበቃ ባለሙያ ተብሎ መደቡ መሰየሙ ፀረ ተባይ ኬሚካልን በሚመለከት ትኩረት ያልተሰጠው ዘርፍ መሆኑ፣ እንዲሁም የፀረ-ተባይ ኬሚካል ስራውን ሊያስራ የሚያስችል በቂ የስው ኃይል አለመኖሩና መዋቅሩም ከፌደራል እስከ ወረዳ ወጥ ሆኖ ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ የሚያሰራ አለመሆኑ፤

55.እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ግብርና ምርት ደህንነትና ብቃት ማረጋገጫ በንግድ ቢሮ ውስጥ መሆኑና ከተማ አስተዳደር ላይ መቆሙ ወደ ታች እስከ ክፍለ ከተማና ወረዳ አለመውረዱ፣

56.በአጠቃላይ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር እና የሰው ሃይል በተደራጀ መልኩ አለመኖሩና ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑ፣ በክልል ደረጃ የፀረ ተባይ ኬሚካል የጥራት ቁጥጥር የሚል መደብ ቢኖርም ወደ ዞንና ወደ ወረዳ ሲወርድ የፀረ ተባይ ኬሚካል የጥራት ቁጥጥር ባለሙያ አለመኖሩ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ መደቡ የኬሚካልና የማዳበሪያ ባለሙያ እንደሚልና ስራውን ደረበው ስለሚሰሩ የፀረ ተባይ ኬሚካል ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመስራት እንደተቸገሩ፣ እንዲሁም መዋቅሩ ከፌደራል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ የተናበበ አለመሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ የዘረጋው የአሰራር ስርዓት እንደሌለ በናሙና ከተመረጡ ክልሎችና መስተዳደሮች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

57.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስራውን ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር አለመኖሩ እና ከሰው ኃይል እጥረት አንፃር ስራዎችን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በኳራንቲን ጣቢያዎች የእፅዋት ተቆጣጣሪ ሰራተኞች የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ተቆጣጣሪ ሆነው በተደራቢ ስራዎችን እየሰሩ መሆናቸው እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅር በኳራንቲን ጣቢያዎች የፀረ-ተባይ ተቆጣጣሪ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

58.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል መዋቅር ባለመኖሩ እና ባለው መዋቅር የተቀመጠውን የሰው ሃይል በስብጥሩ መሰረት የተሟላ ባለማድረጉ ከተማ መስተዳድሮችን፣ ክልሎችን፣ ዞን እና ወረዳዎችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ

ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን በታቀደ፣ ተከታታይነት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንዳያደርጉ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘርፉን ስራ በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት መኖሩን በተመለከተ

59. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን እንዲሁም በተዋረድ የዘርፉን ስራ በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት ሊሟላለት ይገባል፡፡

60. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ የዕፅዋት ኳራንቲን ጣቢያዎቹ በቁሳቁስ ያልተሟሉ /በቂ የግብዓት አቅርቦት/ የሌላቸውና እድሳት የማይደረግላቸው መሆናቸው፤
- ✓ አዳዲስ የኳራንቲን ጣቢያዎች በመግቢያና በመውጫ በሮች አለመቋቋም፤
- ✓ የተለያዩ ወቅታዊ መረጃዎች ሪፖርት ለመሰብሰብና የዕለት ከዕለት ግንኙነትና ክትትል ለማድረግ በኳራንቲን ጣቢያዎቹ የመገናኛ ችግር መኖር (ለምሳሌ ስልክ፣ ፋክስ፣ ኢንተርኔት)
- ✓ በሁሉም ኳራንቲን ጣቢያዎች የቢሮ ጥበት ችግር መኖሩና ጣቢያዎቹ ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ፣ ለመከታተል የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ የተሸከርካሪ እጥረት መኖሩ፤
- ✓ የሞጆ ኳራንቲን ጣቢያ የሚጠቀመው ማህተም የአዲስ አበባንና የአዳማን ኳራንቲን ጣቢያ ማህተም መሆኑ እና የድሬደዋ፣ አዳማ፣ ቦሌና ሞያሌ ኳራንቲን ጣቢያዎች የራሳቸው ፋይናንስ /በጀት/ ሲኖራቸው የሞጆ ኳራንቲን ጣቢያ አለመኖሩ እንዲሁም ኳራንቲን ጣቢያው እራሱን የቻለና በግብዓት የተደራጀ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

61. እንዲሁም የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደር እና ቁጥጥር ስራውን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊያሰራ የሚያስችል በቂና የተሟላ ግብዓት አለመኖሩ፣ በናሙና በታዩ ክልሎች ያለው የፀረ ተባይ ኬሚካል ስርጭትና አጠቃቀም በዕቅድ የተመራ አለመሆን፣

የሚቀርበው ፀረ ተባይ ኬሚካልና የአርሶ አደሩ አጠቃቀም ባለመመጣጠኑ አርሶ አደሩ በህገወጥ ኮንትሮባንድ ነጋዴዎች በድንበር የሚገቡ ምንጫቸው የማይታወቁ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን እንደ አማራጭ የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ፣ ለማሳያ፡- ዲዲቲና ማላታይን እንደ ሀገር የተከለከሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለአዝርት፣ ለጫት፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ በሰፊው እንደሚጠቀሙና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢ የሆነ የቁጥጥር ሥርዓት አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

62. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ እንደ ሚኒስቴር መ/ቤት ከበላይ አመራሩ ጀምሮ ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ እና የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ በዚህም የዘርፉን ስራ በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት እንደሌለው እንዲሁም ድጋፍና ክትትል ማድረግ እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡

63. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ስርዓቱን በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት እንዲሟላ ባለማድረጉ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው በብቃት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይከናወን እና ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር እንዳይደረግ አድርጎታል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በተመለከተ

64. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በእያንዳንዱ የፀረ ተባይ የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አጠቃቀማቸውን ለመከታተል የሚያስችል የፀረ ተባዮችን ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት /በዳታ ቤዝ/ የተደገፈ መረጃ ሊኖረው እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማስገቢያ ፍቃድ አሰጣጥ፣ መስፈርቶች እና እንዳይገቡ የሚከለከሉ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በግልፅ መረጃውን ለተገልጋዩ የሚያሳውቅበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡

65. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው

የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት /ተገልጋዮች/ የመረጃ እና እውቀት ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣
- ✓ በ2009 በጀት አመት 1400 የማስገቢያ ፈቃድ ላይ የሰፈሩ መረጃዎች ወደ ዳታ ቤዝ ለማስገባት ታቅዶ መረጃው ወደ ዳታ ቤዝ የገባላቸው 600 (47%) ብቻ ሲሆኑ ይህም ከዕቅድ ግማሽ በታች መሆኑ፤
- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ወጥነት ያላቸው ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማቶች ተዘጋጅተው ለአበባ እርሻ ልማት ድርጅት እንዲደርሳቸው አለመደረጉ እና የተሟላ መረጃ በቅፆቹ መሰረት ማቅረብ አለመቻላቸው፤
- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስመጪዎችና አከፋፋይ ድርጅቶች የግብዓት ክምችትና የሽያጭ መረጃ መሰብሰቢያ ቅፆቹ ያሞሏቸው መረጃዎች በዳይሬክቶሬቱ ከተያዘው መረጃ ጋር ያለመጣጣም ችግር መታየቱ፤
- ✓ በአዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፋብሪካ የፀረ ተባይ የማቀነባበር፣ የማስመጣትና ቀንሶ ማሸግ ተግባራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እንዲሁም በፋብሪካውና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል ያለው የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩ፣ በተለይም ያለቀለት ምርት አስገብቶ በትንንሽ መያዣዎች አሽጎ ለገበያ ከመቅረብ (Repacking) እና ለዚህም ተግባር ፀረ ተባይ ከውጪ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ (import Permit) እና ከጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ (import authorization Letter) ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ከማግኘት ጋር በተያያዘ መቸገራቸው፤
- ✓ የተቀላጠፈ አሰራርን ለመፍጠር በዘርፉ ስራ የተሰማሩ ድርጅቶችን ታሪክ መዝግቦ ለመያዝ፣ ግልፅ አሰራርን ለመፍጠር፣ ለእያንዳንዱ ተገልጋይ በስሙ ፋይልና መለያ ሰጥቶ በመያዝ፣ ማንኛውም የደብዳቤ ግንኙነት ቅጂው በፋይል እንዲቀመጥ በማድረግ እንዲሁም በተመሳሳይ በሶፍት ኮፒ መረጃዎች እንዲያዙ አለመደረጉ፤
- ✓ የመረጃ ፍሰትን እና በስራ ክፍሉ ሰራተኞች መካከል ያለውን ግልፀኝነትና ተዓማኒነት ይበልጥ ለማጠናከር በፀረ ተባይ ምዝገባና ቁጥጥር የስራ ክፍል

ከኬሚካል ሥራ ጋር አገልግሎት የሚሰጡ ኮምፒውተሮችን በዳታ ቤዝ ማገናኘት አለመቻሉ፤

- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካል ኢንስፔክሽን በማድረግ በየመግቢያ በሮች የሚይዙት መረጃ በተመሳሳይ ቅፅ እንዲጠቀሙ ማድረግና ይህም መረጃ በሶፍት ኮፒ እየተሞላ ለማዕከል እንዲላክ ተደርጎ የማስገቢያ ፈቃድ ለሚሰጠው ክፍል እንዲደርስ ተደርጎ የተጠናከረ መረጃ ቋት እንዲኖር አለመደረጉ፤
- ✓ ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ተጠቃሚ ድርጅት ከውጪ ሀገር ያስገባውን እና ከሀገር ውስጥ የገዛውን፣ የተጠቀመበትን፣ የተረፈውን እና አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ኬሚካሎችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ ሪፖርት አለማቅረቡ፤
- ✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ መረጃዎች በተገቢው ሁኔታ ወደ ኮምፒውተር ገብተውና በሀርድ ኮፒ /መዝገብ/ ተጠናክረው አለመያዛቸው፤
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች፣ ከኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ከአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች እና በዘርፉ ስራ ከተሰማሩ አካላት ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ ክፍተት መኖሩ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ደካማ መሆኑ፤
- ✓ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት /ተገልጋዮች/ የመረጃ እና እውቀት ክፍተት እንዳለባቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

66.የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በእያንዳንዱ የፀረ ተባይ የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አጠቃቀማቸውን በሚመለከት ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት ወይም በዳታ ቤዝ የተደገፈ መረጃ እንደሌለ እና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ እና በተገቢው ሁኔታ እንዳልሰራ ገልፀዋል፡፡

67.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አጠቃላይ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መረጃዎችን ወደ ዳታ ቤዝ ለማስገባትና በማዕከላዊ የመረጃ ቋት ለመያዝ ብቃት ያለው በሙያው የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ እንዲሁም እንደ ሚኒስቴር መ/ቤት ለዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት ስለማይሰራ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች የህይወት ዑደት ደረጃቸውን ጠብቀው መረጃዎች በማዕከላዊ የመረጃ ቋት ወይም በዳታ ቤዝ ተደግፈው እንደማይመዘገቡ እንዲሁም ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ክልል ወጥ የሆነ መዋቅር፣ አቅም ያለው የሰው ኃይል

እና የባለሙያ እጥረት በመኖሩ የፀረ ተባይ ኬሚካል መረጃዎችን ለተገልጋዩ ማሳወቅ እንዳልቻሉ፣ ነገር ግን ከ2005 ዓ.ም ጀምረው በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ ገፅ ላይ እንደሚያስቀምጡ ገልፀዋል፡፡

68.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የህይወት ዑደት ደረጃቸውን ጠብቀው በማዕከላዊ የመረጃ ቋት እና በዳታ ቤዝ የተደገፈ መረጃ ባለመያዙ እና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ባለመደረጉ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡና ወደ ውጭ ሀገር የተላኩ፣ ጥቅም ላይ የዋሉና ያልዋሉ፣ የተከማቹና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በዓይነት፣ በመጠንና በቦታ በተገቢው ሁኔታ እንዳይታወቁ ከማድረጉም በተጨማሪ የሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ የሆኑ አጠቃላይ የፀረ ተባይ ኬሚካል መረጃዎችን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር እንዳይለዋወጡ አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረጉን በተመለከተ

69.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ ውስጥ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ(ጊዜ ያለፈባቸው) ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች በአይነትና በመጠን እንዲሁም በቦታ ተዘርዝረው ሊያዙ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ሊኖረው ይገባል፡፡

70.የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒየኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

71.በሼሚ ፍሎራ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅት አገልግሎት የሰጡ ባዶ የፀረ ተባይ ኬሚካል መያዣ እቅዎች ለረጅም ጊዜ መጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

72. በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤

| ተ.ቁ | ዞን | የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች | ብዛት | መለኪያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ወላይታ | ቲልት 20% E.C | **30** | ሊትር |
| | | ባምፐር 250% E.C | **30** | ሊትር |
| 2 | በደቡብ ኦሞ | ማላታይን 50% E.C | 270 | ሊትር |
| 3 | ዳውሮ | ማላታይን 50% E.C | 800 | ሊትር |
| 4 | ሀድያ | ማላታይን 50% E.C | 427 | ሊትር |
| | | ዳይሜቶኤት | 200 | ሊትር |
| | | ሪችዌይ | 20 | ሊትር |
| | | ባይፊዳን | 240 | ሊትር |
| | | ባምፐር 250% E.C | 416 | ሊትር |
| | | ባይላተር | 970 | ሊትር |
| | | ሱፐር ስታር | 9 | ኪ/ግ |
| 5 | በከምባታ ጠምባሮ | ማላታይን 50% E.C | 254 | ሊትር |
| | | ባይፊዳን | 25.5 | ሊትር |
| | | ቲልት | 32 | ሊትር |
| | | ባይላተን 250 E.C | 91 | ሊትር |
| | | ማላታይን 50% E.C | 69 | ሊትር |
| | | 2-4D | 193 | ሊትር |
| | | ሮገር 40% E.C | 50 | ሊትር |
| | | ሪዶሚል ጎልድ | 4 | ኪ/ግ |
| | | አክታሊክ 2% | 100 | ኪ/ግ |
| 6 | በየም | ማላታይን 50% E.C | 200 | ሊትር |
| | በጉራጌ | --- | 390 | ሊትር |
| 7 | ስልጤ | ሪዶሚል ጎልድ | 6 | ኪ/ግ |
| | | **ጠቅላላ ድምር** | **4,707.5ሊትርእና 119ኪ.ግ** | |

## 73.በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጥቅም የማይሰጡ ባዶ የፀረ ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያዎች የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤

| ተ.ቁ | ዞን | ፀረ ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ናፕሳክ | ሞተራይዝድ | ዩ.ኤል.ቪ |
| 1 | ከፋ | 34 | 11 | --- |
| 2 | ቢንች ማጂ | 36 | 8 | 12 |
| 3 | ወላይታ | 354 | 87 | 26 |
| 4 | ደቡብ ኦሞ | 92 | --- | 10 |
| 5 | ዳውሮ | 29 | 9 | 2 |
| 6 | ሰገን ህዝቦች | 355 | 25 | 231 |
| 7 | ባስኬቶ | 3 | --- | --- |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 8 | ሀድያ | 17 | 20 | 6 |
| 9 | ጉራጌ | --- | --- | 20 |
| 10 | ስልጢ | 73 | 13 | 60 |
| 11 | ሲዳማ | 103 | 39 | 74 |
| 12 | ጌዴኦ | 158 | 9 | 2 |
| 13 | ክምባታ ጠምባሮ | 37 | --- | 1 |
| 14 | የም | 36 | 4 | 5 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | 1,327 | 225 | 449 |

74.እንዲሁም አገልግሎት በመስጠት ላይ ባለው የክልሉ የፀረ ተባይ ማከማቻ መጋዝን ወቅቱ ያለፈበት ማላታይን እየፈሰሰ አፈሩ የረጠበበት ሁኔታ መኖሩ እና አገልግሎት የሚሰጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በኬሚካል በረጠበው አፈር ላይ ተደርድረው ያሉበት ሁኔታ መኖሩ ለመረዳት ተችሏል፡፡



**ፎቶ 1 በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት በክልሉ ግብርና ቢሮ ወቅቱ ያለፈበት ማላታይን እየፈሰሰ አፈሩ በረዘረዘበት መጋዝን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ተደርድረው የሚያሳይ ፎቶ**

75.በተጨማሪም በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በተለያዩ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኖች የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው፣ ባዶ የፀረ ተባይ መያዥያዎች እንዲሁም በፀረ ተባይ ኬሚካል የተበከሉ አፈሮች መኖራቸው፣ ለማሳያ፡-

- ✓ ምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ወረዳ መጋዝን ከ300 ሊትር በላይ 2-4D መኖሩና ይህ ፀረ ተባይ ኬሚካል ከቢሮአቸው ጀርባ መሆኑ በጤናቸውና በስራቸው ላይ ትልቅ ተፅኖ እየፈጠረባቸው መሆኑ፣
- ✓ በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮማቦልቻ ወረዳ መጋዝን በበርሜል ውስጥ 180 ሊትር ማላታይን፣ በመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቶች ህብረት ስራ ዩኒየን Diazol 60E.C 79 ሊትር፣ በቦራ ደንበል የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን Topik 080 E.C 22 ሊትር፣ Mancolaxyl 72% WP 49 ኪ/ግ እና Aeromine 2-4D

amine Salte 2,748 ሊትር፣ ምስራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ ወረዳ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት በመጋዘን ውስጥ ማላታይን መኖሩ ይህ ማላታይን በቢሮአቸው ጎን ያለ እና በስራቸው ላይ ተፅዕኖ እየፈጠረባቸው መሆኑ ማላታይኑ ከ15 አመት በላይ ተዘግቶ በመጋዘን ውስጥ ያለና የሚመለከተው አካል ምንም ዓይት ድጋፍና ክትትል እንዳላደረገላቸው በተጨማሪ አርሲ ነገሌ፣ ዶዶላ፣ ሻላ እና ገደብ ሀስሳ ወረዳዎች ላይ እንደሚገኝ፣ በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ መጋዝን ማተቢ፣ ሲፒ 15፣ ኦሞ ጥቅም የማይሰጡ ባዶ የፀረ ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያዎች በቁጥር 31 መኖሩ፤



**ፎቶ 1 በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮማቦልቻ ወረዳ መጋዝን የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው፣ ባዶ የፀረ ተባይ መያዥያዎችና መርጫ መሳሪያዎች በመጋዝን ውስጥ ተቀላቅለው መቀመጣቸውን የሚያሳይ ፎቶ**

76. በተመሳሳይ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መርጫዎች፣ በርሚሎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች መኖራቸው፣ በተጨማሪም በመጋዘኖች አካባቢ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ለረዥም ጊዜ በበርሜል ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ በርሜሉ የመመረዝ ባህሪ እንደሚያሳይና የመጋዝኑ አፈር እርጥበት በመፍጠር እንደሚበከል፣ ለማሳያ፡- የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እና ባዶ የፀረ ተባይ ኬሚካል መያዥያ እቃዎች፤

77. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | ክልል /ዞን/ወረዳ | የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች | ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | በክልሉ ግብርና ቢሮ | 2-4D | 35ሊትር |
| | | አክተሊክ W.P | 14 ሊትር |
| | | ባይላተን 25% W.P | 50ሊትር |
| | | ቶፐዞል 25% E.C | 58ሊትር |
| | | ቲልት 250% E.C | 5ሊትር |
| | | ፎርማሊ E.C | 34.3ሊትር |
| 2 | አዊ ዞን | ሲቪን 85% E.C | 12 ኪ/ግ |
| | | ማንኮዜብ 80% W.P | 38 ኪ/ግ |
| | | ዲያዚኖን 60% E.C | 149 ሊትር |
| | | ዲያዚኖን 10% P | 14 ኪ/ግ |
| | | ኢንዶ ሰልፋን /ታዩዳን/ 35% E.C | 244 ሊትር |
| | | ማላታይን 50% E.C | 348 ሊትር |
| | | ፌንትሮታይን 50% E.C | 425 ሊትር |
| | | አክታሊክ 2% G | 91ኪ/ግ |
| | | ባይላተን 25% W.P | 25 ኪ/ግ |
| | | ዱርሰባን /ክልሮፓይን/ 48% | 248 ሊትር |
| | | ማርሻል /ካርቦሰላፋን/ 25% E.C | 400 ሊትር |
| | | ባምፐር 25% E.C | 24 ሊትር |
| | | ራወንድ አፕ | 5 ሊትር |
| | | ኢንዶ ሰልፈን 35% E.C | 29 ሊትር |
| | | ፕሪማ ግራም | 10 ሊትር |
| | | ግራንስታር 75% WP | 36 ኪ/ግ |
| | | ኢትዮ ማላታዮን 95% E.C | 17 ሊትር |
| | | ማላታይን 60% E.C | 239 ሊትር |
| | | ዩኒዜብ 80% W.P | 10 ኪ/ግ |
| | | ጋም | 20 ሊትር |
| 3 | ምስራቅ ጎጃም ዞን | ማላታይን 50% E.C | 1071 ሊትር |
| | | አክትሊክ 2% W.P | 213 ኪ/ግ |
| | | ዲያዚኖን 60% | 694 ሊትር |
| | | ሴቨን /ካርባሪን 35% W.P | 383 ኪ/ግ |
| | | ማላታይን 35% E.C | 10 ሊትር |
| | | ባምፐር | 901 ሊትር |
| | | ባፌዳል | 6 ኪ/ግ |
| | | ቲልት | 20 ሊትር |
| | | ማንኮዜብ | 108 ኪ/ግ |
| | | ባይሎቴን | 80 ኪ/ግ |
| | | 2-4D | 448 ሊትር |
| 4 | ማዕከላዊ ጎንደር ዞን | ኢንዶሱልፋን /ታዮኔክስ/ ታዮዳን 35% E.C | 14 ሊትር |
| | | ዱርስባን /ክሎርፐይሪፎስ/ 48% E.C | 100 ሊትር |
| | | ዱርስባን /ክሎርፐይሪፎስ/ 240 ULV | 900 ሊትር |
| | | ማላታይን 95% ULV | 393 ሊትር |
| | | ማላታይን 50% E.C | 2798ሊትር |
| | | ማንኮዜብ 80% W.P | 64 ኪ/ግ |
| | | 2-4D | 306 ሊትር |
| | | አክቴሊክ 2% ዱቄት | 420 ኪ/ግ |
| | | ዲያዚኖን /ባዙዲን/60% E.C | 64 ሊትር |
| | | ኢንዶሱልፋን 5 ዱቄት | 668 ኪ/ግ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ክሩዘር 350 F.C | 15 ኪ.ግ |
| | | አክቴሊክ 50% E.C | 167 ሊትር |
| | | ሴቢን /ካርባሪል 85% W.P | 15 ኪ/ግ |
| 5 | ደቡብ ጎንደር ዞን | ሴቨን 85%E.C | 325.5 ኪ/ግ |
| | | ማንኮዜብ 80%W.P | 138 ኪ/ግ |
| | | ሮገርዳይሚቶት 40%E.C | 793 ሊትር |
| | | ዲያዚኖን 60%E.C | 37 ሊትር |
| | | ዲያዚኖን 10%P | 8 ኪ/ግ |
| | | ኢንዶሰልፋን/ታዩዳን 35%E.C | 295 ሊትር |
| | | ማላታይን 50%E.C | 1272 ሊትር |
| | | 2-4D ፀረ አረም | 107 ሊትር |
| | | አክታሊክ 2%G | 242 ኪ/ግ |
| | | ዱርስባን 240%E.C | 2ሊትር |
| | | ሲምቡሽ /ሳይፐርሜትሪን/ 1%G | 58ሊትር |
| | | ኢትዮላቲዮን/ማላታይን 5%WP | 115 |
| | | ኢንዶሰልፋን 5%WP | 12 |
| | | ቲልት 250%E.C | 203ሊትር |
| | | በምፐር 25%E.C | 24ሊትር |
| | | ዚንክ ፎስፋይድ.P በጣሳ | 40 ኪ/ግ |
| | | ሴልፎን በጣሳ | 1ኪ/ግ |
| | | ሄራዲያን | 38 ሊትር |
| 6 | ሰሜን ጎንደር ዞን | ማላታይን 50% | 1252 ሊትር |
| | | ዱሩሱባን | 240 |
| | | ዩኤልቨ | 200 ሊትር |
| | | አክቲሊክ 2% | 357 ኪ/ግ |
| | | ሴቨን 85% wp | 40 ኪ/ግ |
| | | ማንኮዜብ | 80 ኪ/ግ |
| | | ዳውሊውፒ | 52 ኪ/ግ |
| | | 2 ፎርድ | 317 ሊትር |
| | | አንዳብሪን | 58 ሊትር |
| | | ማላታይን 95% Ec | 73 ሊትር |
| | | ዲያዜብ 60% | 1548 ሊትር |
| | | ዱርሱባን 95%ulv | 170 ሊትር |
| | | ማላታይን 90%E.C | 64 ሊትር |
| 7 | ኀዛምን ዞን | ማላታይን 50% E.C | 220ሊትር |
| | | ማላታይን | 47 ሊትር |
| 8 | ባህርዳር ዙሪያ ወረዳ | ዲያዞናል | 13 ሊትር |
| 9 | ምስራቅ ጎጃም ዞን | ቲልት 250% E.C | 250 ሊትር |
| | | ኢትዮሚራዝ 12.5 E.C | 272 ሊትር |
| | | **ጠቅላላ ድምር** | **17918 ሊትር እና 3481.5 ኪ/ግ** |

78.በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በዞኑ ጥቅም የማይሰጡ ባዶ የፀረ ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያዎች ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | ክልል/ዞን | የመርጫ መሳሪያ ስም | በመጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | በክልሉ ግብርና ቢሮ | ሲ.ፒ 15 | 10 |
| | | አግሮሞንድ | 2 |
| | | ሰሎ /ጀመን/ | 1 |
| | | ሲ.ፒ-3-ኤል | 1 |
| | | ጂዲኤም | 5 |
| | | ሞተራይዝድ | 5 |
| | | ዩኤልቪ | 14 |
| | | ማተቤ | 2 |
| | | ሳይፈን ፓምፕ | 6 |
| 2 | ምስራቅ ጎጃም | ሲ.ፒ 20 | 170 |
| | | ሲ.ፒ 15 | 358 |
| | | ማተቤ | 54 |
| | | ራይንስ | 159 |
| | | ካርፒ | 32 |
| | | ማሞ | 369 |
| | | ማተቤ | 114 |
| | | ቨርቶይድ | 12 |
| | | ዩኤልቪ | 95 |
| | | ዩኤልቪ ማተቤ በባትሪ የሚሰራ | 56 |
| | | ቴክኖማ ሞተራይዝድ | 42 |
| | | ማሩ ያማ | 5 |
| | | አስፒዶ | 8 |
| | | ቴክኖማ ሞተራይዝድ | 85 |
| | | እስፒል | 5 |
| | | ደስተር ማሩ ናካ | 102 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | **1,666** |

79.በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች መኖራቸው፣ ለማሳያ፡- ቃፍታ፣ አዲ ረመፅ፣ ወልቃይት ፀገዴ ላይ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ማላታይን፣ በሁመራ ወረዳ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ማላታይን 53 ሊትር፣ ፌንቶሪታይን 203 ሊትር፣ ሪዳማር 103.5 ኪ.ግ፣ ሞዳን 891.5 ሊትር ኬሚካሎች፣ ባዶ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መያዥያ 30 በርሜሎች ባለ 200 ሊትር እና ባለ 60 ሊትር የሚይዙ መኖራቸው፤

80. በአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማምረቻ ፋብሪካ በድርጅቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንዲሁም ንብረትነቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሆነ ዲዲቲ በድርጅቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ መጋዝን ውስጥ መገኘቱ፣ የላብራቶሪ ኬሚካል መያዣ የነበሩ ባዶ ጠርሙሶች፣ በርሚሎች በፋብሪካው ግቢ ውስጥ በብዛት ተከማችተው መገኘታቸው እና ድርጅቱ በርሚሎቹን ለህብረተሰቡ በሽያጭ መልኩ እንደሚያቀርቡ እና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ እንዳላደረገ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡



ፎቶ 3- በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በአዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ የላብራቶሪ ኬሚካል መያዣ የነበሩ ባዶ ጠርሙሶች፣ በርሚሎች በፋብሪካው ግቢ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በብዛት መከማቸታቸውን የሚያሳይ ፎቶ

81. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ

ካለው የሰው ኃይል እጥረት እና ለፀረ ተባይ ኬሚካሎች ትኩረት ካለመስጠት አንፃር እንደሆነ፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችና መያዣ እቃዎችን በተመለከተ ፕሮፖዛል ለመቅረፅ በሂደት ላይ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

82.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች በአይነትና በመጠን እንዲሁም በቦታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ባለማድረጉ በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በመንግስት፣ በዩኒኖች፣ በማህበራት እና በግል ድርጅት መጋዘኖች በክምችት ላይ ያሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችንና መያዣ እቃዎችን ዝርዝር በተገቢው ሁኔታ ማወቅ እንዳይቻል ከማድረጉም በተጨማሪ በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላትም ይሁኑ ህብረተሰቡ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በጤናቸው ላይ ጉዳት ቢያደርስባቸውም አማራጭ በማጣት በቅርበት አብረው የሚኖሩበት ሁኔታ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡

## <u>ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን መኖሩን በተመለከተ</u>

83.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት አስተማሪ የሆኑ መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን ሊኖረው እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

84.የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡- እንደ ሀገር ስለ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ጠቀሜታ፣ በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ስለሚያስከትለው ጉዳት እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አስተማሪ የሆኑ መልዕክቶች የሚተላለፉበት የሚዲያ ሽፋን አለመኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

85. እንዲሁም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋት እና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ጎጅ ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን እራሱን የቻለ የአየር ሰዓት ተሰጥቶት በሚዲያ እንዲተላለፍ አለመደረጉ፣ ለዘርፉ እንደ ሀገር ትኩርት ያልተሰጠው በመሆኑና የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ አርሶ አደሩ እንደማንኛውም ምግብና መጠጥ ፀረ-

ተባይ ኬሚካሎችን ማየቱና ከምግብ፣ ውሃ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ጋር በመቀላቀል የሚያስቀምጡበት ሁኔታ መኖሩ እንዲሁም ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከተጠቀሙ በኃላ እጃቸውን ሳይታጠቡ ወደ ምግብ የሚሄዱበት ሁኔታ እንዳለ፣ ማሳ ውስጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በመበጥበጥ እርጭት እንደሚያከናውኑ፣ የፀረ ተባይ ኬሚካል እቃዎችን ለዘይት፣ ለፀበልና ውሃ መያዥነት እንደሚጠቀሙባቸው እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚዲያ ሽፋን እንዲኖርና ተግባራዊ እንዲደረግ በተገቢው ሁኔታ እንዳልሰራ /እንዳልፈፀመ/ በኦዲቱ ወቅት በቀረበው ቃለመጠይቅ ገልፀዋል፡፡

86. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአግባቡ ከተጠቀሙባቸው ጠቃሚ እንደመሆናቸው መጠን ባግባቡ ካልተጠቀሙባቸው ደግሞ በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋት እና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ጎጅ ተፅዕኖ ከፍተኛ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ለፀረ-ተባይ ኬሚካል ስራው ትኩረት ባለመስጠቱ እራሱን የቻለ የአየር ሰዓት ተሰጥቶት በሚዲያ እንዲተላለፍ አለማድረጉን ነገር ግን የፀረ ተባይ አደጋዎችንና የስጋት መቀነሻ መንገዶችን በሚመለከት ለአርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደር በሚዲያ እንዲተላለፍ በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

87. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን እንዲኖረው ባለማድረጉ ህብረተሰቡ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ስለሚያስከትሉት ጉዳት ካለው የግንዛቤ እጥረት አንፃር እንደ ሀገር የተከለከሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለአትክልት፣ ፍራፍሬና ለሰብል ምርት፣ በቤት ውስጥ ከተለያዩ ቁሳቁሶች ጋር አብሮ የሚጠቀምበት፣ በገበያ ቦታ ከሸቀጣሸቀጦች ጋር የሚገበያይበት እንዲሁም በፀረ ተባይ ኬሚካል እቃዎች ለመጠጥና ለምግብ መያዣነት የሚጠቀምበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ መግባቱን በተመለከተ

88. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አማካሪ ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ ሊገባ እና ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

89.በኦዲቱ ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

90.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፣ ከጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣ ከኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ ከብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከገቢዎችና ጉምሩክ ሚኒስቴር የተውጣጡ እና የተዋቀሩ የቦርድ አባላት እንደሚኖሩት እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ምዝገባ፣ እድሳት፣ ማገድ፣ ማሻሻል፣ ምዝገባን መሰረዝ፣ የፍቃድ አሰጣጥ መስፈርቶችና ቅድመ ሁኔታዎችን እና ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማስወገድን፣ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አጠቃቀምን፣ አስተሻሸግን፣ መለያ አደራረግን፣ ማጓጓዝን፣ ማከማቸትን፣ ስርጭትን፣ የባዶ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መያዣዎች ማስወገድን እንዲሁም ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንፃር ከመተግበር አኳያ ሚኒስቴር መ/ቤቱን እንደሚያማክር እና በብሔራዊ ደረጃ ከሚወከል አካል ጋር በመተባበር እንደሚሰራ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አዋጅ ላይ ቢገለፅም ቦርዱ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ወደ ስራ አለመግባቱና በተወሰነለት ጊዜም አለመሰብሰቡን ለመረዳት ተችሏል፡፡

91.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አማካሪ ቦርድ እንዳልተቋቋመና በተወሰነለት ጊዜም እንዳልተሰበሰበ እንዲሁም ቦርዱ ባለመቋቋሙ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃላይ ስራዎችን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቦርዱ ጋር በመመካከር እንዳልተሰሩ /እንዳልተፈፀሙ/ ገልፀዋል፡፡

92.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አማካሪ ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ ባለመግባቱ ቦርዱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጣው አዋጅ ቁጥር 674/2002 ዓ.ም የተሰጠውን ዝርዝር ስልጣንና ኃላፊነት እንዳይወጣ ከማድረጉም በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቦርዱ ጋር በመመካከር መስራትና መወጣት ያለበትን ኃላፊነት እንዳይወጣ እንዲሁም የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው በብቃት፣ ቀልጣፋና ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ እንዳይከናወን አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭትላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

93. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭትን በሚመለከት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

94. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ በኮንትሮባንድ የሚገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸው እና ህብረተሰቡ ከህገ ወጥ ነጋዴዎች ገዝተው ምንጫቸው ያልታወቁ እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ የሚረጩበት ሁኔታ መኖሩ ነገር ግን ይህን ችግር ለመቆጣጣር የሚያስችል የተቀናጀ የክትትል ስርዓት አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሳያ ያህል፡-

- ✓ ለወባ መከላከያ ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ዲዲቲ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባና ጥቅም ላይ እንዳይውል የተከለከለ ፀረ ተባይ ኬሚካል ቢሆንም አርሶ አደሩ ለሰብል፣ ለጫት፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ለተባይ መከላከያነት እንደሚጠቀሙበት፤
- ✓ ማላታይንና ዲዲቲ፣ ነጭ ቦለቄ ቡቃያ ላይ የተከሰተውን ተባይ ለመከላከል በሚል በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ቡኖ በደሌ ዞን በዴሳ ከተማ ከሚገኙ ሱቆች ውስጥ ትራይሴል፣ ማላታይን፣ ዲያሞግ 40%፣ ዳይሜቶኤት 40%፣ የታሸገ 500 ግራም የሚመዝን DDT ዱቄት በኮንትሮባንድ በጅጅጋ በኩል በማስገባት የፀረ ተባይ ኬሚካሎች የሚሸጡ እና ህብረተሰቡም ገዝተው የሚጠቀሙ መሆኑ፤
- ✓ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማሸጊያ ላይ ባለው የአጠቃቀም መመሪያ መሰረት እንደማይጠቀሙ እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ተባዩን እስኪገድል ድረስ መጠኑን በመጨመር ደጋግመው እንደሚጨምሩ፤ እንዲሁም አንዱን ኬሚካል ከሌላ ኬሚካል ጋር በመደባለቅ ለምሳሌ፡- ዲዲቲን ከማላታይን ጋር በመቀላቀል በሰብሉ ላይ የሚረጩ መሆኑን፤

- ✓ በሰብል ክምችት ወቅት ለነቀዝ መከላከያ በሚል ዲያዚኖንና ማላታይን ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን እንደሚረጩ፣
- ✓ ተባይ /ነቀዝ/ ሲፈጠር በሴልፎስ /አሉሚኒየም ፎስፋይድ/ እንክብል ካለ ባለሙያ ድጋፍ የማከም ልምድ በአርሶ አደሩ እንዳለ እና የአጠቃቀም ችግር በሰፊው መኖሩና የበቆሎ ሰብል እንዳይነቅዝ በማለት አውድማ ላይ እንደተወቃ በማላታይን በማሸት ወደ ጆንያ እንደሚከቱ፤
- ✓ በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብሮች ውስጥ ጊዜው ያለፈበት ኬሚካል በብልቃጥ እየተቀነሰ ያለምንም አጠቃቀም መመሪያ እንደሚሸጥ፤
- ✓ አርሶ አደሮቹ በቦለቄ ምርት ላይ የዋግ ተባይ ተከሰተም አልተከሰተም ካርባሪል የፀረ ተባይ ኬሚካል እንደሚጠቀሙ እና ፈቃድ ሳይኖራቸው በድብቅ በሚነግዱ ነጋዴዎች አማካኝነት የፀረ ተባይ ኬሚካል ስርጭት መኖሩ፤
- ✓ ህብረት ስራ ማህበራት እና ዩኒየኖች በመጋዝን ውስጥ ያለ ምንም የባለሙያ ድጋፍ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የሚጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩ፤
- ✓ አርሶ አደሩ ለወባ መከላከያ የሚጠቅመውን አጎበር ለምርት መያዣነት እንደሚጠቀሙበትና ካለባለሙያ ምክር በህገወጥ መንገድ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ካገኙበት ሁሉ በመግዛት በራሳቸው ውሳኔ እንደሚጠቀሙ ለማሳያ፡- አትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ በሳምንት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በድግግሞሽ መጠቀማቸው፡፡
- ✓ የወባ መከላከያ ኬሚካሎች ርጭት ሲደረግ በአርሶ አደሩ ክምችት የሚገኝ ምርት ላይ ጥንቃቄ ስለማይደረግ ከምርቶቹ ጋር የመነካካት እድሉ ሰፊ መሆኑ፣ እንዲሁም ቤት ውስጥ ትኋንና ቁንጫ ሲፈጠር ማላታይን ያለጥንቃቄ እንደሚረጩ፣ የተለያዩ ከአገልግሎት የተረፉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እና ባዶ መያዣ እቃዎች ከእህል ምርት ጋር ተቀላቅለው እንደሚቀመጡ እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አቅርቦትና ስርጭት ወጥ አለመሆኑ ለምሳሌ፡- ዩኒየኖች፣ የግል ድርጅቶች፣ መሰረታዊ ማህበራት እንደሚያቀርቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡

95. በተጨማሪም በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ የምርት መለያ ቁጥር 0001036360 እና 0001036401 በ17/10/2012 እና በ25/02/2012 ተመርቶ በ17/10/2014 እና በ25/02/2014 ከ7 ወር እስከ 1 ዓመት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት 19,790 (አስራ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና) ኪሎ ግራም ዳይሜቶኤት ቴክኒካል

/Dimethoate Technical/ ጥሬ ዕቃ በመጠቀም 28,000 /ሀያ ስምንት ሺህ/ ሊትር ዳይሜቶኤት 40% ኢ.ሲ እና 6,000 (ስድስት ሺህ) ሊትር ዳይሜቶኤት 40% ዩ.ኤል.ቪ. በማምረት ለህብረተሰቡና ለአርሶ አደሩ በሽያጭ መልኩ መሰራጨቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

96.በተመሳሳይም በአማራ ቤ/ክ/መንግስት በደቡብ ጎንደር ዞን አርሶ አደሮቹ በህገወጥ የተገዛ 2-4D ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለስንዴና ለገብስ አርም ላይ ይሆናል በሚል ሰብሉን በሚረጩበት ወቅት ምርቱ በአጠቃላይ የጠፋበት ሁኔታ መኖሩ፣ እንዲሁም በባህርዳር ዙሪያ የሚገኙ አርሶ አደሮች በአገር አቀፍ ደረጃ የተከለከሉ ማላታይንና ዲዲቲ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በጫት ማሳ ላይ የሚረጩበት ሁኔታ እንዳለ እና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተገቢው ሁኔታ እንዳልሰራ እና ለተግባራዊነቱ የሚጠበቀውን ድጋፍ እና ክትትል እንዳላደረገላቸው ገልፀዋል፡፡

97.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭትን በሚመለከት በቂ ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉ፣ የችግሮቹ ምክንያት ያለው የሰው ኃይል እና መዋቅር በቂ ስላልሆነ ስራዎችን መስራት እንዳልቻሉና ለአርሶ አደሮቹ እስከታች የወረደ በቂ ግንዛቤ ባለመስጠታቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ካለምንም ባለሙያ ድጋፍና መመሪያ እየተጠቀሙ ያሉበት ሁኔታ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

98.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭትን በተገቢው ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ባያቸው የሀገሪቱ ክፍሎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡና ምንጫቸው ያልታወቁ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የሚሰራጩበት፣ የሚጠቀሙበትና የሚከማቹበት ሁኔታ እንዲፈጠር ከማድረጉም በተጨማሪ ህገ ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝውውር እንዲስፋፋ አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

99.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

100. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

✓ በፀረ ተባይ ኬሚካል አቅራቢዎች መጋዘን ውስጥ ተባይ ሲከሰት ያለ ምንም ጥንቃቄ እና የባለሙያ እገዛ ጤናቸውን በሚጎዳ መልኩ ሲልፎስ በተባለ ኬሚካል የማከም ልምድ መኖሩ እና ከሴልፎስ ኪኒን በተጨማሪ ማላታይን በመበጥበጥ ምርት በያዘ ጆንያ ላይ እንደሚረጩ እንዲሁም የቁንጫ፣ የትኋን ማጥፊያ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በቦለቄ ምርት ላይ የሚረጩበት ሁኔታ እንዳለ በተጨማሪም አርሶ አደሩ በዕፅዋት ምርት ላይ ለጤና እጅግ አደገኛ የሆኑና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ማላታይን፣ ዲዲቲና 2-4D መጠቀም ካለባቸው በላይ እና በመደጋገም እንደሚረጩ ለመረዳት ተችሏል፡፡

101. በአዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማምረቻ ፋብሪካ ድርጅት ዙሪያ ያለው ማህበረሰብ የእኔነት ስሜት በድርጅቱ ላይ እንዲኖረው በሚል እሳቤ እስከ አራት ኪሎ ማላታይን በማመልከቻ እንደሚሰጥ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

102. ህብረተሰቡ በጤናውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በሚያስከትል መልኩ በገበያ ቦታዎችና በተለያዩ የመንገድ ዳሮች ላይ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን እያቀናነሱ የሚሸጡበት ሁኔታ መኖሩ እና እንደ ሀገር ለፀረ ተባይ ኬሚካሎች ያለው የግንዛቤ እጥረት አነስተኛ በመሆኑ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝና አጠቃቀም በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ እየተጠቀሙ እንዳሉና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ምንጫቸው ያልታወቁና ያልተመዘገቡ በህገወጥ ነጋዴዎች ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ተሰራጭተው መገኘታቸው፤




ፎቶ 4-በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በአዳማ ከተማ ፀረ ተባይ መሸጫ መደብር ከሆቴል ጎን መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ

103. በአማራ ብ/ክ/መንግስት በደቡብ ጎንደር ዞን የፀረ ተባይ ኬሚካሎች የአቅርቦት እጥረት አለ በሚል የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ዲያዚኖን 60% እና ቲልት ለአርሶ አደሩ እንደሚያሰራጩ እንዲሁም  አርሶ አደሮች የፀረ-ተባይ ኬሚካል መርጫ መሳሪያዎችን በወራጂ ወንዝ እንደሚያጥቡና ከታች ያለው ሌላው ህብረተሰብ ወንዙን ለመጠጥ፣ ለልብስ ማጠቢያና ለተለያዩ ለቤት ውስጥ አገልግሎቶች የሚያውሉበት ሁኔታ መኖሩ፤

104. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡና ምንጫቸው ያልታወቁ በኮንትሮባንድ በህገወጥ ነጋዴዎች የሚገቡ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአትክልት፣ ፍራፈሬ፣ ጫት እንዲሁም በግብርና ምርቶች ላይ ያለምንም የባለሙያ እገዛ የሚረጩበት ሁኔታ መኖሩ፣ በቤት ውስጥ የሰው ልጆችን በሚጎዳ መልኩ ከምግብና መጠጦች ላይ አብረው ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በመደባለቅ የሚስቀምጡበት፣ በፀረ ተባይ ኬሚካል መያዥ እቃዎችን ለቤት ውስጥ ቁሳቁስ እንደሚጠቀሙባቸው፣ በገበያ ቦታዎች እንደ ፍራፍሬና የምግብ ምርቶች ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በተለያዩ እቃዎች እያቀናነሱ የሚሸጡበትና የሚገዙበት ሁኔታ እንዳለ፣




**ፎቶ 5-በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በዱግዳ ወረዳ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በገበያ ቦታዎችና በመንገድ ዳር እየተቀናነሱ ሲሸጡ የሚያሳይ ፎቶ**

105. በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በዱግዳ ወረዳና በአዳሚ ቱሉ ጂዱ ኮምቦልቻ ወረዳ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ጽ/ቤት ለረጅም አመታት በፀረ ተባይ ማከማቻ መጋዝኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸውና የኬሚካሎቹ ሽታ በስራ ቦታቸው እና በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ እያሳደረባቸው መሆኑ፣ በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ በተገቢው ሁኔታ እንዳልሰራ /እንዳልፈፀመ/ እና ለተግባራዊነቱ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር እንዳላደረገ ገልፀዋል፡፡

106. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ በቂ፣ በእቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጋቸውና ህብረተሰብ ካለው የግንዛቤ እጥረት አንፃር እንዲሁም በዚህ ዙሪያ እስትራቴጅ ባለመቀረፁ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ ጎጂ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆኑ፣ ነገር ግን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሀገሪቱ ውስጥ እያሳደሩ ያሉትን ጎጅ ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችል ፕሮጀክት ተቀርፆ ለልማት አጋራት ቢቀርብም ምላሽ አለመሰጠቱን ገልፀዋል፡፡

107. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችል ተገቢውንና ለውጥ

ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ በዘርፉ ስራ ላይ ያሉ ሰዎች እየተጎዱ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ የዕፅዋት ውጤቶች ከኤክስፖርት ምርት ውጪ እየሆኑ ያሉበት ሁኔታ መኖሩና በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የንብ ምርት ውጤቶች እንዲቀንሱና እንዲጠፉ ሊያደርገው እንደሚችል ይገመታል፡፡

## <u>ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የመሸጡ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ</u>

108. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች መሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

109. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒየኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት የሚከተሉት ታይተዋል፡-

- ✓ በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብሮች /ድርጅቶች/ ውስጥ በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የሚጠይቀውን የሙያ መስፈርት ያላሟሉ እና ከሙያው ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው በመምህርነት፣ በአካውንቲንግ እና በሌሎች ተዛማጅነት በሌላቸው የስራ ዘርፎች የሰለጠኑ ሰዎች ሲሆኑ ነገር ግን የፀረ ተባይ ኬሚካሎችን የሚሸጡበት ሁኔታ መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡
- ✓ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከ1,000 (አንድ ሺህ) በላይ ህገወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካል ቸርቻሪዎች መኖራቸው፣
- ✓ የኦዲት ቡድኑ በናሙና ባያቸው የሀገሪቱ ቦታዎች በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጥ ስራ ላይ ለመሰማራት መጀመሪያ በዶክመንት ደረጃ የዘርፉ አካላት ህጋዊ የሆነውን መስፈርት አሟልተው የብቃት ማረጋገጫ ከወሰዱ በኃላ ወደ ስራው ሲገቡ ግን በመሸጫ መደብር ሱቆች በሙያው ያልሰለጠኑና ያልተመረቁ ሰዎች፣ ሴቶችና ህፃናት እንዲሸጡ ባይመከርም የሚሸጡበት ሁኔታ መኖሩ፣ እንዲሁም በሸቀጣሸቀጥ መሸጫ ሱቆች /መደብሮች/ ውስጥ የተለያዩ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በመቀላቀል እንደሚሸጡ፣ እነዚህን

አካላት ለመቅጣትና ለመቆጣጠር አስገዳጅ ህግና የአሰራር መመሪያ ባለመውጣቱ ለመቅጣት እንደተቸገሩና ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው አካላት በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብሮች ውስጥ እየሸጡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱንና ተግባራዊ አለማድረጉን ገልፀዋል፡፡




ፎቶ 6-ብደ/ብ/ብ/ክ/መንግስት ወንዶ ገነት ወረዳ በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብር የፀረ ተባይ ኬሚካሎች እየተቀናነሱ ሲሸጡ የሚያሳይ ፎቶ

110. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ እስከ ወረዳ ድረስ አደረጃጀቱን ተከትሎ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ፣ ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ የፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡

111. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች መሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ባለመቻሉ በዘርፉ ያልሰለጠኑ ሰዎች ለደህንነታቸው በሚያሰጋ መልኩ በስራው ላይ የተሰማሩ ሲሆን ስለሙያው የሚያስፈልገው ገለፃ ሳይሰጥ ለህብረተሰቡ በሽያጭ እንዲቀርብ በማድረግ ህብረተሰቡም ካለምንም የባለሙያ ትዕዛዝ እና የአጠቃቀም መመሪያ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ገዝቶ በመጠቀሙ በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋትና በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዲያስከትል አድረጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ በተመለከተ

112. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው መዝግቦ በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ በማድረግ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን ስርዓት ሊዘረጋ እና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

113. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

114. በ9 ክልሎችና በ1 ከተማ መስተዳደር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ዲዲቲ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፤

| ተ.ቁ | ክልል /መስተዳድር/ | መጋዝኖች | ብዛት | መለኪያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በድሬደዋ መስተዳድር | 1 | 4,793 | ኪ/ግ |
| 1 | በአማራ ብ/ክ/መንግስት | 102 | 287,861.60 | ኪ/ግ |
| 2 | በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት | 190 | 286,747.50 | ኪ/ግ |
| 3 | በትግራይ ብ/ክ/መንግስት | 30 | 28,953.67 | ኪ/ግ |
| 4 | በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት | 68 | 203,231.50 | ኪ/ግ |
| 5 | በሐረሬ ብ/ክ/መንግስት | 1 | 5,440 | ኪ/ግ |
| 6 | በቤንሻንጉል ብ/ክ/መንግስት | 17 | 17,433.24 | ኪ/ግ |
| 7 | በአፋር ብ/ክ/መንግስት | 16 | 16,349.60 | ኪ/ግ |
| 8 | በጋምቤላ ብ/ክ/መንግስት | 4 | 43,074 | ኪ/ግ |
| 9 | በሱማሌ ብ/ክ/መንግስት | 31 | 34,625.2 | ኪ/ግ |
| | **ጠ/ድምር** | **460** | **928,509.31** | **ኪ/ግ** |

115. በጄኔራል ኬሚካልስ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል/ማህበር የመጠቀሚያ ጊዚ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | ፀረ ተባይ | ብዛት | የሚያበቃበት ቀን |
|---|---|---|---|
| 1 | Current 8EC | 3122ሊትር | 25/5/2015 |
| 2 | Mitigan 18.5EC | 2078ሊትር | 11/2013 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | LOC Chalk | 4992በቁጥር | 1/2014 |
| 4 | LAMDEX 5%EC | 35ሊትር | 8/03/2014 |
| 5 | IPPON 500SC | 1200ሊትር | 11/03/2013 |
| 6 | PYRUS 400SC | 436ሊትር | 11/03/2013 |
| 7 | Pride | 30ሊትር | 11/02/2013 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **6901 ሊትር/ እና 4992ኪ.ግ** | |

116. በተጨማሪም በድርጅቱ 4,767 ሊትር መጠን ያለው ወቅቱ ያለፈበት ፀረ ተባይ ኬሚካል በክምችት መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡

117. በደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት 4,715.5 ሊትር ፈሳሽ ፀረ ተባይ ኬሚካል እና 119 ኪ/ግ ዱቄት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸው እንዲሁም በክልሉ መጋዝን ከ10 ዓመት በላይ በመጋዝን ውስጥ በበርሚል የተቀመጠ ማላታይን መኖሩ፤



**ፎቶ 7-በደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ግብርና ቢሮ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኑ በመኖሪያ ሰፈር፣ በበቆሎ ማሳ አጠገብ መሆኑንና የተለያዩ የቢሮ ንብረቶች ወደ ኬሚካል መጋዝኑ ሲገቡ የሚያሳይ ፎቶ**

118. በኦሮሚ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባሉ 11 ወረዳዎች ጊዜው ያለፈበት ፀረ ተባይ ኬሚካል እና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የታገዱ ኬሚካሎች ቁጥጥር፣ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት አለመኖሩ፣ ለማሳያ፡- ቤንዶካርፕ እና ፕሮፓክሱር ፀረ ወባ ኬሚካሎች በየዓመቱ ሲረጩ ከርጭት የተረፈ ኬሚካል፣ ከሰልና አመድ በመቀላቀል ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር እንደሚያስወግዱ እንዲሁም በአዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮማቦልቻ ወረዳ መጋዝን በበርሚል ውስጥ 180 ሊትር ማላታይን፣ በሻሽመኔ ወረዳ መጋዝን ከ300 ሊትር በላይ 2-4D፣ በመቂ ባቱ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቶች ህብረት ስራ ዩኒየን Diazol 60E.C 79

ሊትር፣ በቦራ ደንበል የገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኒየን Topik 080 E.C 22 ሊትር፣ Mancolaxyl 72% WP 49 ኪ/ግ እና Aeromine 2-4D amine Salte 2748 ሊትር መኖሩ እንዲሁም በቦራ፣ ቦሰት እና ግምቢቹ ወረዳዎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸው፣ ምስራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ ወረዳ ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ጽ/ቤት የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት ማላይታይን ሲኖር ይህ ማላታይን ከ15 አመት በላይ ቢሮ አጠገብ ባለ የሌሎች ንብረቶች መጋዝን ውስጥ የተቀመጠና በጤናቸው ላይ ትልቅ ችግር እየፈጠረባቸው መሆኑ፤





ፎቶ 8- በኦሮሚ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሻሸመኔ ወረዳ መጋዝን የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ለብቻው በተከለለ ቦታ አለመቀመጡንና ከተለያዩ የቢሮ ንብረቶች ጋር በተበታተነ መልኩ የተቀመጠ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ

119. በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በክልሉ 29,510 ሊትር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸው፤

120. በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በቃፍታ፣ አዲ ረመፅ፣ ወልቃይት ፀገዴ ላይ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ማላታይን እንዳሉ፣ በሁመራ ወረዳ የመጠቀሚያ ጊዜ

ያለፈባቸው ማላታይን 53 ሊትር ፣ ፌንቶሪታይን 203 ሊትር፣ ሪዳማር 103.5 ኪ.ግ፣ ሞዳን 891.5 ሊትር ኬሚካሎች መኖራቸው፤

121. በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ማምረቻ ፋብሪካ አገልግሎት የሚሰጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የመጠቀሚያ ጊዜ ካለፈባቸው የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተቀላቅለውና አብረው ተደርድረው መገኘታቸው፣ በድርጅቱ መጋዝን ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው Mancoze.b.80% WP 2006.5 k.g እና Diamethoate Technical18,125 k.g ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸው እንዲሁም ንብረትነቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሆነ 455,249.8 ኪ/ግ ዲዲቲ በድርጅቱ መጋዝን ውስጥ እንደሚገኝ፤



ፎቶ 9- በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ማምረቻ ፋብሪካ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጥቅም ከሚሰጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተቀላቅለው የሚያሳይ ፎቶ

122. በተጨማሪ በድርጅቱ መጋዝን የሚገኙ ሌሎች የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጥሬ ዕቃና ምርቶች ዝርዝር፤

| ተ.ቁ | የጥሬ ዕቃው ስም | መጠን በኪ/ግ | የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃበት |
|---|---|---|---|
| 1 | ዳይሜቶት ቴክኒካል | 17,980 | ኦክቶበር 2014 |
| 2 | ቦሪክ አሲድ | 1,009 | ፌብሪዋሪ 2013 |
| 3 | ካልሲየም ሊግኖሰልፎኔት | 3,475 | ፌብሪዋሪ 2013 |
| 4 | ዲስፐርሳንት ኤች ኤስ | 291 | ኦክቶበር 2010 |
| 5 | ኢ.መልስፋየር ኤም 270-1 | 1,472 | ፌብሪዋሪ 2013 |
| 6 | ዲስፐርሳንት ኤን | 4,854 | ፌብሪዋሪ 2013 |
| 7 | 1,2-ፕሮፓይሊን ግላይኮል | 899 | ፌብሪዋሪ 2013 |
| 8 | አንቲ ኦክሲዳንት | 327 | ማርች 2013 |
| 9 | ሃይ ቦይሊንግ አራማቲክ ሶልቨንት | 35,381 | ሜይ 2013 |
| 10 | ኢ.መልስፋየር ሲኤፍ 971ቢ | 368.2 | ኦገስት 2013 |
| 11 | ኢፒክሎሮ ሃይድሪን | 127 | ዲሰምበር 2014 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12 | ዱዋኖል ዲፒኤም | 5,352 | ሜይ 2014 |
| 13 | ሰርፋክታንት ቢ | 150 | ሜይ 2015 |
| 14 | ማንኮዜብ 80% ደብሊው ዲፒ | 1,980 | ኦገስት 2014 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **73,665.2** | |

123. በሀገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ፀረ-ተባይ ኬሚካል ያለበት መ/ቤት ስም | የኬሚካሉ መጠ /በሊትር/ |
|---|---|---|
| 1. | የአዲስ አበባ ግብርና ቢሮ | 400 |
| 2. | አፋር ብ/ ክ/ መንግስት ግብርና ቢሮ | 5,120 |
| 3. | የግብርና ግብዓት አቅራቢዎች ድርጅት | 39,913 |
| 4. | አዳሚ ቱሉ ፀረ ተባይ ማምረቻ ድርጅት | 540,854 |
| 5. | ባይስም ኃ/የተ/የግ/ማህበር | 1000 |
| 6. | ቤንሻንጉል ብ/ ክ/ መንግስት ግብርና ቢሮ | 14,200 |
| 7. | የኢትዮጲያ የግብርና ስራዎች ኮርፓሬሽን | 24,853 |
| 8. | ጋምቤላ ብ/ ክ/ መንግስት ግብርና ቢሮ | 5,905 |
| 9. | ጀነራል ኬሚካል ኃ/የተ/የግል ማህበር | 10,000 |
| 10. | ሐረር ብ/ክ/ መንግስት ግብርና ቢሮ | 1000 |
| 11. | ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | 480,000 |
| 12. | የኦሮሚያ የህብረት ስራ ማህበር | 42,000 |
| 13. | የኦሮሚያ ብ/ ክ/ መንግስት ግብርና ቢሮ | 58,300 |
| 14. | ሲንጀንታ ኃ/የተ/የግል ማህበር | 3,438 |
| 15. | ዝዋይ ማረሚያ ቤት | 1,920 |
| 16. | ትግራይ ብ/ ክ/ መንግስት ግብርና ቢሮ | 32,000 |
| 17. | ስኳር ኮርፓሬሽን | 100,527 |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **1,397,730 ሊትር** |

124. እንዲሁም ከላይ በናሙና በተገለፁ ሁሉም የሀገሪቱ ቦታዎች የሚገኙ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ለብቻቸው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው እና በየቦታው በተበታተነና ባልተደራጀ መልኩ እንደሚገኙ በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገዱበትን ስርዓት አለመዘርጋቱ እና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡

125. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ወደ ውጭ ሀገር ሄደው በከፍተኛ ገንዘብ ስለሚወገዱ እና ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ በዚህ ዙሪያ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ስለሌሉ እንዲሁም ፕሮጀክት ከመቅረፅ አንፃር የባለሙያ እጥረት በመኖሩ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው በተከለለለት ቦታ በመሰብሰብ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ በማስቀመጥ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን ስርዓት እንዳልዘረጉ እና አፈፃፀሙን ሊከታተሉና ሊቆጣጠሩ እንዳልቻሉ ገልፀዋል፡፡

126. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው በመሰብሰብ በተከለለለት ቦታ ባለማስቀመጡ እና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን ስርዓት ባለመዘርጋቱ እንዲሁም አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ባለመቻሉ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ተበታትነው ለጤና አስጊ በሆነ ሁኔታ ተከማችተው እንዲገኙ እንዲሁም በሰዎችና እንስሳት ጤና፣ በአፈርና በከርሰ ምድር ውሃ ብክትለት ላይ ያለው ስጋት አሳሳቢ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ ለህገ ወጥ ፀረ ተባይ ነጋዴዎች በር እንዲከፍት ያደርገዋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፀረ ተባይ ኬሚካል ሰራተኞች ደህንነት እንዲጠበቅ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

127. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ለሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት እንዲጠበቅ አስፈላጊውን የመከላከያ ትጥቆችን ስለማቅረባቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

128. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒየኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

- ✓ በኳራንቲን ጣቢያዎች የሰራተኞች የራስ ደህንነት መጠበቂያ ትጥቅ መጓደል፣ ወደብ ላይ ስራው በባህሪው የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ንክኪ የሚያጋልጥ ቢሆንም አስፈላጊው የመከላከያ ትጥቆች አለመሟላታቸው፤
- ✓ በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፋብሪካ በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ የሚሆን አልባሳት በአግባቡ እንደማይጠቀሙና ለሰራተኞች ደህንነት የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑ፣
- ✓ በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብሮች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ምንም ዓይነት የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆችን እንደማይጠቀሙ፣ አርሶ አደሮቹ በአዝርት፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ሲረጩ፣ በቤት ውስጥ ያለ ምንም የአጠቃቀም መመሪያ የግብርና ምርቶቹን /በቆሎ፣ ስንዴ፣ ማሽላ፣ ቦለቄ/ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ሲያክሙና ሲያሹ የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆችን አለመጠቀማቸው፣ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ድርጅቶች፣ የመንግስት መ/ቤት የመጋዝን ሰራተኞች፣ የዩኒየኖችና የማህበራት የፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝን ሰራተኞች፣ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅት ሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆች እንደማይቀርቡላቸውና ያለውንም እንደማይጠቀሙ እንዲሁም በገበያ ቦታዎችና በተለያዩ የመንገድ ዳሮች በህገወጥ ኮንትሮባንድ ነጋዴዎች ምንጫቸው ያልታወቁና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ህብረተሰቡና አርሶ አደሩ በብልቃት እያቀናነሱ ሲሸጡና ሲገበያዩ የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆችን እንደማይጠቀሙ እና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንዳላደረገ ገልፀዋል፡፡



ፎቶ 10- በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ዱግዳ ወረዳ በፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች እና በአማራ ብ/ክ/መንግስት ደብረታቦር ከተማ በመሸጫ መደብር ምንም ዓይነት የራስ ደህንነት መጠበቂያ ሳይጠቀሙ የሚያሳይ ፎቶ

129. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የመከላከያ አልባሳት ከፍተኛ ቀረጥ የተጣለባቸው በመሆኑ ከአስፈላጊነታቸውና ወሳኝነታቸው አንፃር ከቀረጥ ነፃ የሚገቡበት ሁኔታ ቢኖር ነገር ግን ካለው የሰው ኃይል እጥረት እና ለዘርፉ ትኩረት ካለመስጠት አንፃር በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ለሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት እንዲጠበቅ አስፈላጊውን የመከላከያ ትጥቆችን ስለማቅረባቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉ ገልፀዋል፡፡

130. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ለሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት መከላከያ ትጥቆችን ስለማቅረባቸው ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ከፀረ ተባይ ኬሚካል ጋር ንክኪ ስላላቸው በጤናቸው ላይ ጉዳት እንዲያስከትልና ለአደጋ እንዲጋለጡ ከማድረጉ በተጨማሪ ሰራተኞች በስጋት ውስጥ ሆነው ስራቸውን ስለሚያከናውኑ ሀገሪቷ አምራች የሰው ሃይል እንድታጣ ሊያደርጋት ይችላል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

131. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የፅሁፍ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

132. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

- ✓ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መቂና ዝዋይ አካባቢ አላግባብና በህገወጥ መንገድ ፀረ ተባይ ኬሚካል እየሸጡ የሚገኙትን የፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብሮች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩልም ይሁን በክልሉ በተጠናከረ መንገድ ቁጥጥር እንደማይካሄድ፣ ያልተመዘገቡ እና ምንጫቸው ያልታወቁ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ያለመቆጣጠር እንዲሁም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ክትትል አለመደረጉ፤
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች ከውጪ አስመጥተው የሚጠቀሙትን እና የቀረውን የኬሚካል መጠን ለመቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት አለመዘርጋቱ እንዲሁም ከድርጅቶቹ በህገ ወጥ መንገድ እየወጡ ያሉትን የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ቁጥጥር አለማካሄዱ፤
- ✓ በኳራንቲን ጣቢያዎች በአካል በመገኘት በዕቅድ የተመራና ተከታታይነት ያለው በቂ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የፅሁፍ ግብረ መልስ የማይሰጥ መሆኑ፤
- ✓ በሀገሪቱ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፤
- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከውጪ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እስከ ተጠቃሚው እስከሚደርሱ ድረስ ያለው የቁጥጥር ስርዓት አለመዘርጋቱ፤

- ✓ አብዛኞቹ አትክልትና ፍራፍሬ የሚያመርቱ አርሶ አደሮች ምንጫቸው ያልታወቁ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከህገወጥ ነጋዴዎች እየገዙ እንደሚጠቀሙና በዚህ ዙሪያ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓቱ ደካማ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

133. እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት ድንገተኛና ወቅታዊ በሆነ ጉዳይ ድጋፍና ክትትል ከማድረግ ውጭ በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ክትትልና ቁጥጥር እንዳላደረገላቸው እና የፅሁፍ ግብረ መልስ እንዳልሰጣቸው ገልፀዋል፡፡

134. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ካለው የሰው ኃይልና የግብዓት እጥረት አንፃር ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን ወቅታዊ እና ድንገተኛ ክትትልና ቁጥጥር ከማድረግ ውጭ በቂ፣ በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንዳለደረጉና የፁሁፍ ግብረ መልስ እንዳልሰጡ ገልፀዋል፡፡

135. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላትን በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደር እና ቁጥጥር ስራው በብቃት፣ ቀልጣፋና ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ እንዳይከናወን አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልታሸገና መለያ ያልተደረገበትን ፀረ ተባይ ኬሚካል ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

136. ማንኛውም አካል ያልታሸገና መለያ ያልተደረገበትን ፀረ ተባይ ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ እንዳያስገባ፣ እንዳያከማች፣ እንዳያጓጉዝ እና ለሽያጭ እንዳያቀርብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

137. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ አዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፋብሪካ Endosulfan Technical ፀረ ተባይ ኬሚካል ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ሞጆ ደረቅ ወደብ ሲደርስ የመጣው Endosulfan Technical ሌብል ላይ የተመረተበት እና የመጠቀሚያ ጊዜ የሚያበቃበት መረጃ የሌለው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

138. እንዲሁም የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከላይ ሌብላቸውን /መለያቸውን/ በመቀየር ስላላቸው ጥራት፣ መጠን፣ ብዛት፣ ተቀባይነት፣ ምንጭ፣ ባህርይ እና ውህድ በተሳሳተ መንገድ ለህብረተሰቡ እና ለአርሶ አደሩ ጥቅም እንዲሰጡ መደረጉ፣ ለማሳያ፡-

- ➢ **ፉንጎዜብ/ Fungozeb80%**

  አስመዝጋቢው Lion International Trading Pvt.Ltd.Co.

  ፀረ-ተባዩ የተመዘገበበት ዓላማ ለ/For the control of late blight on potato/ (በድንች ላይ ለሚከሰት ዋግ /በሽታ/ ለመከላከል) ሌብሉ ተቀይሮ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው

  ለቲማቲም------------- 2.3 kg/h

  ለድንች------------------2.3 kg/h

  ለካሮት-------------------2.3 kg/h

  ሽንኩርት-----------------2.3 kg/h

  ወይን---------------------2.3 kg/h

  ሙዝ---------------------2.3 kg/h

  ፓፓያ--------------------2.3 kg/h

  ጥራጥሬ------------------2.3 kg/h

  ትንባሆ-------------------2.3 kg/h

  ማንጎ---------------------2.3 kg/h

  አፕል---------------------2.3 kg/h

  አርናሜንታል-------------2.3 kg/h

  በሚል ለሽያጭ መቅረቡ

- ➢ **ትራይሴል / Tricel/**

  አስመዝጋቢው Rangvet Pvt.Ltd.Co

  ፀረ-ተባዩ የተመዘገበበት ዓላማ ለ/ For the control of termite in pepper/ (በቃሪያ /በርበሬ/ ላይ ለሚከሰት በሽታ ለመከላከል)

ሊብሉ ተቀይሮ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው

ለቢራቢሮ -----------------------------2kg/h

ለቲማቲም------------------------------2kg/h

ትላትል---------------------------------2kg/h

ገብስ-----------------------------------2kg/h

ለስንዴ---------------------------------2kg/h

በሚል ለሽያጭ መቅረቡ፤

➢ **ማትኮ/ Matco/**

አስመዝጋቢው Markos private limited company

የተመዝገበው ለ /For the control of late blight disease( phytophtora infestans) on potato and tomato and downy mildew (Pernospora destructor) on onion./ (በድንችና ቲማቲም ላይ ለሚከሰት ዋግ/በሽታ/ እና በቀይ ሽንኩርት ላይ ለሚከሰት ሻጋታ ለመከላከል)

ሊብሉ ተቀይሮ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው

ለባቄላ --------------------------------2.5 kg/1000Li/h

ለጎመን--------------------------------2.5 kg/1000Li/h

ለስናፍጭ--------------------------------2.5 kg/1000Li/h

ለሽንኩረት--------------------------------2.5 kg/1000Li/h

ለድንች--------------------------------2.5 kg/1000Li/h

ሉል ዘንጋዳ--------------------------------2.5 kg/1000Li/h

በርበሬ--------------------------------2.5 kg/1000Li/h

ወይን--------------------------------2.5 kg/1000Li/h

በሚል ለሽያጭ መቅረቡ፤

➢ **ሳሪካስ/ sarikas/**

አስመዝጋቢው Issachor Agro Input Importer and Distributor PLC

የተመዝገበው For the control of cabbage aphids on cabbage (በጎመን ላይ የሚከሰት በሽታን ለመከላከል)

ሌብሉ ተቀይሮ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው

ለፋረንሳይ ባቄላ ----------------------1L/h

ቲማቲም --------------------------------1L/h

ድንች -----------------------------------1L/h

በሚል ለሽያጭ መቅረቡ፤

- **ማንኮላክሲል/ Manolaxyl 72% wp/**

  አስመዝጋቢው General chemical and Trading pvt.co

  የተመዘገበው ለ For the control of late blight on tomato (በቲማቲም ላይ ለሚከሰት ዋግ/በሽታ/ ለመከላከል) ሌብሉ ተቀይሮ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ለቲማቲም፣ ለድንች ለርበሬና ወይን በሚል ለሽያጭ መቅረቡ፣ የንግድ ውድድርን በሚሻማ እና ላንድ በሽታ የተመዘገበ ፀረ-ተባይ ኬሚካልን ለሁሉም በሽታ እንደሚሆን በማስመስል መድሃኒት የመላመድ ባህርይን በሚፈጥር መልኩ እየተሰራ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

139. ምንጫቸው ያልታወቁ መለያ የሌላቸው እንዲሁም መለያቸው በአማረኛና በእንግሊዘኛ ያልተፃፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰፊው በህገወጥ ነጋዴዎች አገር ውስጥ ገብተው የሚከማቹበት፣ የሚጓጓዙበት፣ እየተቀናነሱ ለሽያጭ የሚቀርቡበትና ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ መኖሩና በፀረ ተባይ መሸጫ መደብር ሱቆች በድብቅ ለአርሶ አደሩ መለያቸው በእንግሊዘኛ ብቻና በአረበኛ ቋንቋ የተፃፉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በብልቃጥ እየተቀነሱ እንደሚሸጡ፣

140. እንዲሁም በትግራይ ብ/ክ/መንግስት ሰሜን ምዕራብ ዞን ቃፍታ ወረዳ በሱዳን በኩል በህገወጥ ነጋዴዎች መለያቸው /ሌብሉ/ በግልፅ የማይታወቅ፣ ከላይ ሌብሉ / መለያው/ ተነስቶ ሌላ መለያ የሚለጠፍባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንደሚገቡ፣ በሞጆ ደረቅ ወደብ፣ በቦሌ ካርጎ እና በአዳማ እፅዋት ኳራንቲን ጣቢያዎች ለአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች ሌብላቸው /መለያቸው/ በእንግሊዘኛ ብቻ የሆኑ እና ያልተመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገቡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ትዕዛዝ እንደሚሰጣቸው፣ ነገር ግን ባልታወቀ ምክንያት እነዚህ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በአርሶ አደሮቹ እጅ እንደሚገኙ እና አርሶ አደሮቹም ለአትክልትና ፍራፍሬ በማሳ ላይ

እንደሚረጩትና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን ገልፀዋል፡፡

141. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ተቋማዊ አደረጃጀትና የሰው ሃይል ባለመኖሩ እንዲሁም ለዘርፉ ትኩረት ባለመሰጠቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉ በዚህም ያልታሸጉና መለያ ያልተደረገባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበት፣ የሚከማቹበት፣ የሚጓጓዙበት እና ለሽያጭ የሚቀርቡበት ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡

142. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልታሸጉና መለያ ያልተደረገባቸው ከላይ ሌብላቸው በአማረኛና በእንግሊዘኛ ያልተፃፈባቸው፣ ሌብላቸው ተነስቶ በሌላ ቋንቋ ሌብሉ የተተካበት ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ መደረጉና በተገቢው ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉ በሀገሪቱ ውስጥ በህገወጥ መንገድ በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት እንዲበራከቱ ከማድረጉ በተጨማሪ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ፍቱንነት፣ ደህንነት እና ጥራታቸው ስለማይታወቅ ለሰው ልጆችና ለእንስሳት ጤና፣ ለዕፅዋት እንዲሁም ለአካባቢ ጎጂ ተፅዕኖ እንዲፈጥር አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

143. በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

144. የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሂዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡትን ኬሚካሎች በጋራ መቆጣጠርና ስርዓት ማስያዝ ባለመቻሉ ከታለመለት አላማ ውጭ በመዋል

በሰው፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚፈጠረው ጉዳትና ብክለት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መምጣቱ፣ ለማሳያ፡- ሀይድሮጅን ፐርኦክሳይድ ኬሚካል ሀውስ ዌር ማርት ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሌላ ተግባር በሌላ መ/ቤት ፈቃድ ያስመጣውን ኬሚካል ለእርሻ ስራ በማዋል ላይ መገኘቱ፤

- ✓ በአማራ ብ/ክ/መንግስት ምንጃር፣ ሸዋ ሮቢት፣ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጅማ፣ ሻሸመኔ፣ በሶማሌ ብ/ክ/መንግስት እና በሐረሪ ብ/ክ/መንግስት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን እና ለወባ መከላከያነት የሚረጨውን ቤንድዮካርብ ኬሚካል ህብረተሰቡ ከተፈለገው አገልግሎትና አላማ ውጭ ለጫት፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ እየረጨ ያለበት ሁኔታ መኖሩን፤
- ✓ አርሶ አደሮቹ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በህጋዊ መንገድ ያገኙትንም ሆነ ምንጩ የማይታወቅ ከህገወጥ ነጋዴዎች የሚገዙትን ፀረ ተባይ ኬሚካል ያለምንም የአጠቃቀም መመሪያና የባለሙያ ድጋፍ አንዱን ከሌላኛው ፀረ ተባይ ኬሚካል ጋር በመቀላቀል /ከ7-8 ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን/ ከታለመለት አላማ ውጭ በሰፊው እንደሚጠቀሙ፣ ለማሳያ፡- ማላታይንና ዲዲቲ ለአዝርቶች፣ ለጫት፣ ለአትክልት እና ፍርፍሬ የሚጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ✓ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት በዝዋይ ባቱ ወረዳ ለቡና ምርት የሚሆነውን ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለስንዴ ይሆናል በሚል የስንዴ ምርቱን በሚረጩበት ወቅት ሙሉ ለሙሉ ከጥቅም ውጪ የሆነበት ሁኔታ መፈጠሩ እንዲሁም በአማራ ብ/ክ/መንግስት በባህርዳር አካባቢ ራውንድሀፕ ሰብል ከመዘራቱ በፊት አረምን ለማጥፍት የሚረጭ ፀረ ተባይ ኬሚካል ቢሆንም አርሶ አደሩ ለሰብል ምርት በመርጨቱ ሰብሉ ሙሉ ለሙሉ የጠፋበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ✓ አርሶ አደሩ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን ፈሳሽ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የመጠቀሚያ ጊዜ የሚያልፍባቸው ሲጠጥሩና ወደ ስኳርና ጨው መሰል ባህሪ ሲቀየሩ እንጂ የመጠቀሚያ ጊዜ አላለፈባቸውም በሚል በግብርና ምርቶች ላይ የሚጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ✓ በሞጆ ደረቅ ወደብ፣ እና በቦሌ ኳራንቲን ጣቢያዎች በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አስመጭ አካላት ከተመዘገበበት ዓላማ ውጭ የሆኑ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ይመጡና ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የሚጠየቅበት ሁኔታ መኖሩ፣ ለማሳያ፡- በሞጆ ደረቅ ወደብ መካባ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አስመጭ

ድርጅት ዳይካል/ dical/ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ሰፋፊ የቅጠል አረሞችን መከላከል የሚችል ነገር ግን ከተመዘገበበት ዓላማ ውጭ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ እና ማሽላ እንዲሁም ቋሚ  ተክሎች ላይ ለምሳሌ፡- ቡና የመሳሰሉት አርሞችን ይከላከላል በሚል ፀረ-ተባይ ኬሚካሉ ወደ ሀገር ውስጥ በ09/01/2010 ዓ.ም መግባቱ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር እንዳላደረገ ከላይ በናሙና በተገለፁ ሁሉም የሀገሪቱ ቦታዎች የሚገኙ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ገልፀዋል፡፡

145. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ በቂ የሰው ኃይል እና ግብዓት ባለመመደቡ በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ በቂ ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉ እንዲሁም የስራ አፈፃፀም ክፍተት እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

146. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሰዎችና እንስሳት ጤና ላይ ጉዳት የሚደርስበት፣ የተለያዩ የአዝርት ምርቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች ከጥቅም ውጭ እየሆኑ የሚወገዱበት እና በውጭ ሀገራት ተቀባይነት እንዲያጡ እንዲሁም በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዲያሳድሩ አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን መከታተል እና መቆጣጠሩን በተመለከተ

147. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ እና ፈቃድ ያልተሰጣቸውን ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን የሚከታተልበት እና የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

148. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው

የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

149. በኮንትሮባንድ በህገወጥ ነጋዴዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እንዲሁም ሀገር ውስጥ የሚመረቱ ጥራታቸው ያልተረጋገጠ ያልተመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መበራከት፣ ለማሳያ፡-

**ማጂክ ጄል**/ Magic Gel/

- ✓ በአዳማና ቢሾፍቱ ከተሞች በሚገኙ የፀረ ተባይ መሸጫ መደብሮች ውስጥ በስፋት ተሰራጭቶ የተገኘ፣ በህብረተሰቡ በኩል በጣም ተፈላጊ እንደሆነ እና አምራቹ / አስመጭ ካምፓኒው/ አለመገኘቱ፣ ለቸርቻሪ ነጋዴዎች እየተሰራጨ ያለው በህገወጥ ደላላ ነጋዴዎች አማካኝነት እንደሆነና የደላሎችን ማንነት አለመታወቁ፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሉ በሀገር ውስጥ ዓለም ገና በሚባል አካባቢ ትልቅ ፋብሪካ ከፍቶ እየተመረተ መሆኑ ቢታወቅም በተደጋጋሚ ፋብሪካውን ለማግኘት የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ማግኘት አለመቻሉን ለመረዳት ተችሏል፡፡

**የአይጥ መርዝ**/ Mouse Killer/

- ✓ በከፍተኛ መጠን ተስራጭቶ የሚገኝ ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ኬሚካል / የአይጥ መርዝ/ እንደሆነና በተለይም በአዳማ ከተማ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ሱቆች እና በመርካቶ አካባቢ በከፍተኛ ሁኔታ ተስራጭቶ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ካራጂን** / Coragrn 20 SC/ **እና ሬድ ካት**/ Red cat/

- ✓ በአበባ እርሻ ልማት ስራ ስም የገቡ ነገር ግን በንግድ ስራ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እንደሆኑ እና በአዳማ ከተማ ገደብ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ ሱቅ ውስጥ ለሽያጭ ቀርበው መገኘታቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

**ቴምፓ**/ Tempo Sc/

- ✓ ያልተመዝገበ ፀረ-ተባይ ኬሚካል እንደሆነና በመርካቶ ዋዳ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብር ውስጥ መገኘቱ፣ ባለ መደብሮቹ ፀረ-ተባይ ኬሚካሉን ከህገወጥ ደላሎች እንደሚያገኙት ለመረዳት ተችሏል፡፡

150. እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡና ምንጫቸው ያልታወቁ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በህገ ወጥ ነጋዴዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት፣ የሚከማቹበት፣ የሚከፋፈሉበት፣ የሚሸጡበት እና ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ መኖሩ፣ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር

ውስጥ ቢያስገቡም ባልታወቀ ምክንያት በህብረተሰቡና በአርሶ አደሩ እጅ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መገኘታቸው፣ በድብቅ እነዚህን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ያለ ምንም የአጠቃቀም መመሪያና የባለሙያ ድጋፍ በግብርና ምርቶች፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ላይ በሰፊው እንደሚጠቀሙ፣ በአማራ ብ/ክ/መንግስት የእፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ባለስልጣን ሲገናል ፀረ-ተባይ ኬሚካል ሳይመዘገብ በገበያ ላይ በመሸጥ ላይ እያለ መያዙ፣ በደቡብ ጎንደር ዞን ክሮፕ ላውንች 11 ንጥረ ነገሮችን የያዘ ያልተመዘገበ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለማግኘት መቻሉ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ በተገቢው ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር እንዳላደረገ ገልፀዋል፡፡

151. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ለዘርፉ ትኩረት ባለመስጠታቸው፣ በቂ የሰው ኃይልና ግብዓት ባለመመደቡ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች መበራከታቸውንና በተገቢው ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉ ገልፀዋል፡፡

152. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሌላቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ እንዲሁም ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን በተገቢው ሁኔታ ሊከታተልና ሊቆጣጠር ባለመቻሉ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ምንጫቸው ያልታወቁና ህገወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝውውርን እንዲጨምር ከማድረጉ በተጨማሪ ሀገር ውስጥ የሚመረቱ ደህንነታቸውና ጥራታቸው ያልተረጋገጠ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንዲበራከቱ አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የተሰራላቸው መሆኑን በተመለከተ

153. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የተሰራላቸው፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳትና ውሃ ከሚገኝበት ቦታ የራቁ ስለመሆናቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

154. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው

የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የተሰራላቸው፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳትና ውሃ ከሚገኝበት ቦታ የራቁ መሆን እንዳለባቸው ቢታወቅም ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑ ለማሳያ፡- ፍሬንድሺፕ አበባ እርሻ ልማት ድርጅት፣ ኢትዮ ድሪም ፍላወር፣ ብሌን ፋርም፣ ድሬ ኃይላንድ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ያልተሰራላቸው መሆኑ፤
- ✓ የዘራ ኢንጂነሪንግና ማኑፋክቸሪንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር ከ15/05/2007 ዓ.ም ጀምሮ የግብርና ምርት ኬሚካሎችና ለአይጥ መግደያ የሚውል ዘራ ማውስ ኪለር ፀረ ተባይ ኬሚካል በማምረት ላይ ቢሆንም እስከ 26/07/2010 ዓ.ም ድረስ በአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የተረጋገጠ የዘራ ማውስ ኪለር የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ የሌለው እንደሆነና የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኑ፣ ኬሚካል ማምረቻው እና ቢሮው አንድ ቤት ውስጥ ተጠቃሎ የሚገኝ መሆኑን ታውቋል፡፡

155. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ በናሙና ባያቸው የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ያልተሰራላቸው መሆኑ እና በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ቢሆንም ያለው ነባራዊ ሁኔታ ግን በናሙና በታዩት በሁሉም ድርጅቶች የፀረ ተባይ ኬሚካሎች መጋዝን መስፈርቶችን ያላሟሉ መሆኑ፣ ለፀረ ተባይ ኬሚካል ተብለው እራሳቸውን ችለው ባልተገነቡ መጋዘኖች ውስጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ከተለያዩ የቢሮ እቃዎች፣ ማዳበሪያዎች፣ አዝዕርቶች፣ አገልግሎት ከማይሰጡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጋር ተቀላቅለው የሚቀመጡ መሆኑ፣ የፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብር መጋዝኖች እራሳቸውን ችለው የተገነቡ ያልሆኑና በሰዎች መኖሪያ ቤት አካባቢ፣ በሸቀጣሸቀጥ መሸጫ መደብሮች፣ በምግብና መጠጥ ቤቶች እንዲሁም ከእንስሳትና ውሃ ከሚገኝበት ቦታ አካባቢ የሚገኙ መሆናቸው፣ የፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በመሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት መስፈርቱን አሟልተው የብቃት ማረጋገጫ ቢሰጣቸውም የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝናቸው ግን እዛው ኬሚካል በሚሸጡበት ሱቅ ጀርባ ሆኖ በበር ብቻ የሚለያይ መሆኑ፣ በአማራ ብ/ክ/መንግስት በባህርዳር ዙሪያ ያሉ የዩኒየኖች እና

ማህበራት መጋዘኖች መስፍርቱን ያላሟሉ መሆናቸው እና በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን ገልፀዋል፡፡

156. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የፀረ ተባይ ኬሚካል ፍቃድ ከሚሰጡ አካላት ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አሰራር የላላ /ደካማ/ መሆኑ፣ ለዘርፉ ትኩረት አለመስጠታቸው፣ በቂ የሰው ኃይልና ግብዓት ባለመመደቡ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመሰራታቸው በፊት መስፈርቱ የሚጠይቀውን ያላሟሉ እንደሆኑና ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉ ገልፀዋል፡፡

157. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመሰራታቸው በፊት መስፈርቱ የሚጠይቀውን ስለማሟላታቸው ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ ድጋፍና ክትትል ባለማድረጉ የፋብሪካዎች ቦታና መጋዘኖቹ ሰዎች፣ እንስሳት፣ ውሃ ከሚገኝበት ቦታ ያራቁ መሆኑ እንዲሁም በሀይቆች፣ በወንዞችና በከርሰ ምድር የሚገኝ ውሀ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንዲበከል ያደርገዋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

158. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ካሉ መጋዘኑን ወይም የመሸጫ ቦታውን ሊያሽግ እና ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

159. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተመደበ ተቆጣጣሪ በስራ ሰዓት ያለማስጠንቀቂያ የስራ መታወቂያውን በማሳየት ፀረ ተባይ ኬሚካል በማስመጣት፣ በመላክ፣ በማምረት፣ በማሸግ፣ እንደገና በማሸግ፣ መለያ ምልክት በማድረግ፣ በማከማቸት፣ በመሸጥ፣ በማከፋፈል፣ በማስተዋወቅና በመጠቀም ተግባር ላይ የተሰማሩትን ተቋሞች እና የህገወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መጋዘኖችን በየጊዜው የመቆጣጠር እንዲሁም የተከማቸ ፀረ ተባይ ኬሚካል ወይም ፀረ ተባይ ኬሚካሉ የተከማቸበት ሁኔታ ከማናቸውም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከወጣው አዋጅ ድንጋጌ ጋር የማይስማማ ሆኖ ሲገኝ የፀረ ተባይ መጋዘኑን ወይም የመሸጫ ቦታውን እንደሚያሽግ ቢገልፅም፣

160. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

- ✓ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በመቂ፣ ዝዋይ እና ወንዶ አካባቢ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች እየተቀናነሱ እዛው በመደብሮች ውስጥ በሰፊው እየተሸጡ መሆናቸው ለማሳያ፡- ሊንሳሞ ጋቲሳ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ፣ ጌቱ ፋይሳ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ፣ ኤልሻዳይ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ፣ ሶሬቲ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ እና ማሙሽ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ ላይ የተለያየ አይነት ፀረ-ተባይ ኬሚካልዎች( prove, calcinit TM፣ agro feed plus 12፡10፡8+TE) የሚሸጡ መሆናቸው፣
- ✓ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት እና በአዲስ አበባ መስተዳድሮች በህገ ወጥ የተገኙ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ለማሳያ፡- በመቂ ከተማ ናትናኤል ፀረ ተባይ መሸጫ alligator 1.9 EC, tutan 36% SC፣ ማሙሽ ፀረ ተባይ መሸጫ tutan 36% SC፣ ጌቱ ፈይሳ ፀረ ተባይ መሸጫ prove፣ በቀለ መልከቶ ፀረ ተባይ መሸጫ tutan 36% SC፣ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ራዛ ፀረ ተባይ መሸጫ ቶፕ ህገ ወጥ ፀረ ተባይ የትኳን ማጥፊያ መገኘቱ፤
- ✓ በአዳሚ ቱሉ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፋብሪካ የመጠቀሚያ ጊዜው ከ1-40 ቀን ያለፈው 8,160 ኪ/ግ ማንኮዜብ ፀረ ተባይ ኬሚካል ለሽያጭ መቅረቡ እና ገዥዎቹ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈ እንደሆነ ድርጅቱ እየገለፀላቸውና በፊርማቸው እያረጋገጡ እንደሚገዙ፣ ድርጅቱ በቤተ ሙከራ የጥራት ደረጃውን ሳያረጋግጥ በህገወጥ መንገድ ለገበያ ማቅረቡ፤
- ✓ ኮማንዶ/ Comando እና ሬድ ካት ፀረ ተባይ ኬሚካሉ /ፀረ-አይጥ/ በከፍተኛ ደረጃ በሸቀጣሸቀጥ መሸጫመደብሮች ውስጥ በብዛት እየተሸጠ እንደሚገኝ፣ ፀረ ተባይ ኬሚካሉን ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ያደረገው ራንግ ቬት ፒ.ኤል፣ሲ እንደሆነ እና ይህ ኬሚካል በአዳማ ከተማ ዋርካ ፀረ-ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብር ውስጥ መገኘቱ፣ የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት እንደሆነ እና ፀረ ተባይ

ኬሚካሉ /ፀረ-አይጥ/ በትንንሽ ማሸጊያዎች እስከ 10 ግራም ድረስ እየተቀናነሰ እንደሚሸጥበት ሁኔታ መኖሩ፤

- ✓ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከላይ በተገለፁት ሁሉም ቦታዎች ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር አድርጎ እርምጃ አለመወሰዱን ለመረዳት ተችሏል፡፡

161. በተጨማሪም በናሙና በታዩ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸውንና በተገቢው ሁኔታ ባለመያዛቸው እየፈሰሱ ያሉበት ሁኔታ መኖሩ በፀረ ተባይ ኬሚካል መሸጫ መደብሮች፣ በዩኒየኖች እና በማህበራት መጋዝኖች ውስጥ ህገወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ቢኖሩም ሚኒስቴር መ/ቤቱ መጋዝኑን ወይም የመሸጫ ቦታውን እንደማያሽግ እና ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርግ ገልፀዋል፡፡

162. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ የፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝኖችና የመሸጫ መደብሮች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መኖራቸውን ሆኖም መጋዝኖቹንና የመሸጫ ቦታዎቹን እንዳሸጉ ነገር ግን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንዳላደረጉ ገልፀዋል፡፡

163. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ይበሉ እንጂ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝኖች እና በመሸጫ መደብሮች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በየትኛው የሀገሪቱ ክፍል እና መቼ ስለማሸጋቸው ወይም እርምጃ ስለመውሰዳቸው የሚገልፅ ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ ባለመቅረቡ የተሰጠው መልስ ለኦዲቱ አጥጋቢ አይደለም፡፡

164. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዘኖችና የመሸጫ መደብሮች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ሲያገኝ መጋዝኑን ወይም የመሸጫ መደብሩን ባለማሸጉ እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ በመጋዝኖቹ ውስጥ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የመፍሰስ አደጋ ቢያጋጥም በአፋጣኝ አደጋውን ለመከላከል አስቸጋሪ ከማድረጉ በተጨማሪ በህገወጥ ግለሰቦች አማካኝነት የሚካሄደውን የፀረ ተባይ ኬሚካል ግብይት እንዲስፋፋ እና ህጉን

ተላልፈው በሚያገኛቸው ሰዎች ላይ ክስ ለመመስረት በአዋጅ የተሰጠውን ግዴታና ኃላፊነት ባለመወጣቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው ውጤታማነቱን የጠበቀ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠቱን እና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ

165. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችን፣ ከተማ አስተዳደሮችን እና በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን እንዲሁም ለህብረተሰቡ በቂ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሊሰጥና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

166. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ በፀረ-ተባይ አጠቃቀም፣ በፀረ-ተባይ አመራረጥ፣ በፀረ-ተባይ አይነቶች እና ባህሪያቸው በየወቅቱ እና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እማይሰጡ መሆኑ፤
- ✓ ለኳራንቲን ጣቢያ ሰራተኞች ተከታታይነት ያለው የክህሎት ማሻሻያ፣ የፀረ ተባይ አሰራር፣ ሌብል እና ምልክቶች፣ የልምድ ልውውጥ፣ የስጋት ትንተና፣ አጠቃላይ ዓለም አቀፍና ሀገራዊ የህግ ማዕቀፎች፣ የኢንስፔክሽን ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነትን ጨምሮ ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች አንፃር ታይቶ የማብቃት ስልጠናዎች፣ የላብራቶሪ እቃዎችና አሰራር ስርዓትን፣ በመስክ ላይ የተባይና የበሽታ ልየታን በተመለከተ ስልጠናዎች አለመሰጠታቸው፤
- ✓ ለልማት ጣቢያ ባለሙያዎች በፀረ ተባይ ቅሪት ዙሪያ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች አለመሰጠታቸው፤
- ✓ ከአርሶ አደሩ ምርት ገዝተው የሚከዝኑ ድርጅቶች ብቃት ባላቸው አካላት በፀረ ተባይ የማከም ስራውን እንዲያከናውኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና አለመሰጠቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

167. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ድንገተኛ እና ወቅታዊ የሆኑ ስልጠናዎችን ከመስጠቱ ውጭ በቂ፣ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና አለመስጠቱ እንዲሁም ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን ገልፀዋል፡፡

168. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ስልጠናዎችን እንሰጣለን ነገር ግን የሚሰጡ ስልጠናዎች በቂ፣ ተከታታይነት ያላቸው እንዳልሆኑ እንዲሁም ለተግባራዊነታቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንደማያደርጉና አፈፃፀሙ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

169. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ በቂ፣ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ባለመስጠቱ እና ለተግባራዊነቱ ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው በኳራንቲን ጣቢያዎች በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙ አካላት በብቃት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይከናወን ከማድረጉ በተጨማሪ ህብረተሰቡ ካለው የግንዛቤ እጥረት አንፃር ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ በአዝርት ምርቶች፣ በአትክልትና ፍራፍሬዎች ላይ አንዱን ፀረ ተባይ ኬሚካል ከሌላኛው ፀረ ተባይ ኬሚካል ጋር በመደባለቅ እንዲሁም መጠቀም ካለበት ውጭ በመደጋገምና አብዝቶ የሚጠቀምበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጎታል፡፡

## <u>ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት በቅንጅት መስራቱን እና የመግባቢያ ሰነድ መፈራረሙን በተመለከተ</u>

170. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና በዘርፉ የሚሰሩ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ስራው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን በቅንጅት ሊሰራና የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ይገባል፡፡

171. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ

በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒየኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሂዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ መሰረት፡-

- ✓ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ህገወጥ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ዝውውርን ለመቀነስ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያካተተ የጋራ መድረክ መፍጠር፣ አፈፃፀሙን መከታተልና የህግ ማዕቀፉን ማጠናከረ አለመቻሉ፤
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ከክልሎች፣ ከአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች እና በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው ከሚገኙ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ መሆኑ፤
- ✓ በ2009 በጀት አመት ህገ- ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካል ቁጥጥርን አጠናክሮ ለመስራት ከኦሮሚያ፣ ከትግራይ፣ ከአማራ እና ከደቡብ ብ/ብ/ ህዝቦች ብሄራዊ መንግስታት እና ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ጋር የመግባቢያ ስነድ ለመፈራረም ታቅዶ አለመከናወኑ፤
- ✓ የፀረ ወባ እና የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ርጭት ላይ የግብርና እና የጤና ጥበቃ መ/ቤቶች በጋራ ተቀናጅተው የመስራት ክፍተት በሰፊው መኖሩ፤
- ✓ ህገ ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ንግድን ለመቆጣጠር ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር የላላ መሆኑ፤
- ✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ክልል ወርዶ ከአርሶ አደሩ ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ፤
- ✓ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ንግድ ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ፤
- ✓ የፀረ ወባ ኬሚካሎች ሲረጭ በሰብል ላይ የኬሚካል ቅሪት በመገኘቱ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ቅንጅታዊ አሰራሩ ደካማ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

172. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ጎጅ ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን እና እንደ ሀገር ለዘርፉ ትኩረት ካለመሰጠቱ አንፃር የሚመለከታቸውን ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ስራው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን በቅንጅት አለመሰራቱና የመግባቢያ ሰነድ /የጋራ እቅድ/ እንዳልተፈራረመ ገልፀዋል፡፡

173. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ከሚመለከታቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እንደማይሰሩ እንዲሁም የመግባቢያ ሰነድ ወይም የጋራ እቅድ እንደማይፈራረሙ ገልፀዋል፡፡

174. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች፣ ከከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም በዘርፉ ከሚሰሩ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በጋር የማይሰራ፣ የመግባቢያ ሰነድ የሌለው መሆኑ ለፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው ውጤታማነት እንቅፋት የሆኑ ተግዳሮቶች ማለትም የአፈፃፀም ደንብ፣ መመሪያና እስታንዳርዶች፣ የግንዛቤ ክፍተቶች እንዲሁም ከፌደራል ጀምሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያለውን መዋቅርና የሰው ሃይል ለመቅረፍ የሚደረገውን ጥረት ውጤታማና የተሳካ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ቆጠራ በማድረግ መወሰድ ያለበትን መነሻ ሀሳብ ማዘጋጀቱን እና ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረቡን በተመለከተ

175. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ቆጠራ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መወሰድ ያለበትን እርምጃ መነሻ ሀሳብ ሊያዘጋጅ እና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

176. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የአማራ፣ ትግራይ፣ ደቡብ እና ኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ስምንት ዞን፣ ዘጠኝ ወረዳዎች፣ አንድ የከተማ መስተዳድር፣ ስምንት ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ ሶስት የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ ሁለት በዘርፉ ስራ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኔኖች፣ በማህበራት፣ ሁለት የባለድርሻ አካላት ባካሄዳቸው የዶክምንቴሽን ክለሳዎች፣ የመስክ ምልከታዎች፣ ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በተሞላ ቼክ ሊስት መሰረት፡-

- ✓ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች በክልል፣ ዞንና ወረዳ ባሉ መጋዝኖች፣ በአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ በፀረ ተባይ ኬሚካል በማስመጣት ስራ ላይ በተሰማሩ አካላት፣ በዩኒየኖች፣ በማህበራት መጋዝኖች በብዛት ቢኖሩም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቆጠራ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መወሰድ ያለበትን እርምጃ መነሻ ሀሳብ አለመዘጋጀቱ እና ለሚመለከታቸው አካላት አለማቅረቡን ገልፀዋል፡፡

177. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ፣ ለኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ለረቂቅ የኦዲት ሪፖርቱ በሰጡት መልስ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ማከማቻ ማዕከላዊ መጋዝን በሚኒስቴር መ/ቤት ደረጃ ስለሌለ ኬሚካሎቹን ቆጠራ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንደማይሰሩ ገልፀዋል፡፡

178. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ቆጠራ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መወሰድ ያለበትን እርምጃ መነሻ ሀሳብ ባለማዘጋጀቱ እና ለሚመለከታቸው አካላት ባለማቅረቡ በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች አይነታቸው፣ መጠናቸውና ብዛታቸው በማይታወቅ፣ በተበታተነና ጉዳት በሚያደርስ መልኩ ተከማችተው ከመገኘታቸው በተጨማሪ ለገበያ እየቀረቡና ህብተረሰቡ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎቹን የሚገበያይበት እና ጥቅም ላይ የሚያውልበት ሁኔታ እንዲፈጠር አድርጎታል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የኦዲቱ መደምደሚያ (Audit Conclusion)

የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደር እና ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ የሚከተሉት ግፈቶች ኣና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡

179. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኦዲቱ እስከተደረገበት ቀን ድረስ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን ለመተግበር የሚያስችለው ደንብ፣ መመሪያ እና እስታንዳርድ የለውም እንዲሁም አፈፃፀማቸውን ሊከታተልና ሊቆጣጠር አልቻለም፡፡

180. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነታቸውንና ጥራታቸውን በላብራቶሪ መርምሮና አረጋግጦ አልመዘገበም፡፡

181. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በግብርና ምርቶች ላይ ሊኖር የሚችል የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ የለውም፣ ተግባራዊም ኣላደረገም፡፡

182. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በማስመጣት ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ሳይመዘገቡና ፍቃድ ሳያገኙ ሲያስተዋውቁ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ኣላደረገም፡፡

183. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተገቢው ሁኔታ የሚሰጥበት ስርዓት አልዘረጋም፡፡

184. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ያላቸው እና ከተመረቱ 6 ወር ያላለፈባቸው ስለመሆናቸው በተገቢው ሁኔታ ኣላረጋገጠም፡፡

185. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኘውን የዘርፉን ስራ ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር የለውም፣ የሚጠይቀውንም የሰው ሃይል በስብጥሩ መሰረት ኣላሟላም፡፡

186. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን እንዲሁም በተዋረድ የዘርፉን ስራ በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት የለውም፡፡

187. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማስገቢያ ፍቃድ አሰጣጥ፣ የማስገቢያ መስፈርቶች እና እንዳይገቡ የሚከለከሉ ፀረ-ተባዮች በቅድሚያ በግልፅ መረጃውን ለተገልጋዩ በተገቢው ሁኔታ አላሳወቀም፣ ተግባራዊም አላደረገም፡፡

188. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በእያንዳንዱ የፀረ ተባይ የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አጠቃቀማቸውን ለመከታተል የሚያስችል የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት እና በዳታ ቤዝ የተደገፈ መረጃ የለውም እንዲሁም በተገቢው ሁኔታ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ አያደርግም፡፡

189. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ ውስጥ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች በአይነትና በመጠን እንዲሁም በቦታ እየተዘረዘሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ በተገቢው ሁኔታ አላደረገም፡፡

190. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት አስተማሪ የሆኑ መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን የለውም፡፡

191. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አማካሪ ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ አልገባም፣ በዓመት አራት ጊዜም አልተሰበሰበም፡፡

192. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና ስርጭትን በሚመለከት በተገቢው ሁኔታ አልሰራም /አልፈፀመም/፣ ለተግባራዊነቱም ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

193. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ መቀነስ በሚያስችል መልኩ በተገቢው ሁኔታ አልሰራም፡፡

194. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች መሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን በተገቢው ሁኔታ አላረጋገጠም፣ ተግባራዊም አላደረገም፡፡

195. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ በማድረግ አግባብ ካላቸው

አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን ስርዓት አልዘረጋም እንዲሁም አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር አልቻለም፡፡

196. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ለሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት እንዲጠበቅ አስፈላጊውን የመከላከያ ትጥቆችን ስለማቅረባቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

197. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላትን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም እንዲሁም የፅሁፍ ግብረ መልስ አልሰጠም፡፡

198. ማንኛውም አካል ያልታሸገና መለያ ያልተደረገበትን ፀረ ተባይ ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ እንዳያስገባ፣ እንዳያከማች፣ እንዳያጓጉዝ እና ለሽያጭ እንዳያቀርብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

199. በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በተለያዩ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር አልተደረገም፡፡

200. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን በተገቢው ሁኔታ ሊከታተልና ሊቆጣጠር አልቻለም፡፡

201. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዘኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የተሰራላቸው፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳትና ውሃ ከሚገኝበት ቦታ የራቁ ስለመሆናቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

202. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዘኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ካሉ መጋዘኑን ወይም የመሸጫ ቦታውን እንደማያሽግ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

203. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላትን በቂ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና አልሰጠም፣ ለተግባራዊነቱም ክትትልና ቁጥጥር አላደረገም፡፡

204. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና በዘርፉ ስራ ላይ የሚሰሩ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ስራው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን በቅንጅት አልሰራም እንዲሁም የመግባቢያ ሰነድ /የጋራ ዕቅድ/ አልተፈራረመም፡፡

205. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ቆጠራ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መወሰድ ያለበትን እርምጃ መነሻ ሀሳብ አላዘጋጀም እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት አላቀረበም፡፡

# ክፍል አራት

## የኦዲቱ ማሻሻያ ሀሳብ (Audit Recommendation)

206. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን ለመተግበር የሚያስችለው ደንብ፣ መመሪያ እና እስታንዳርድ ቢያዘጋጅና አፈፃፀሙን ለውጥ ሊያመጣ ቢሚያስችል መልኩ ቢከታተልና ቢቆጣጠር የዘርፉ ስራ በብቃት፣ቀልጣፋና፣ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲያከናውን ያደርገዋል፡፡

207. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነትና ጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን በላብራቶሪ መርምሮና አረጋግጦ ቢመዘግብ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋት እና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ጎጅ ተፅዕኖ እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡

208. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በግብርና ምርቶች ላይ ሊኖር የሚችል የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ ቢኖረውና ተግባራዊ ቢያደርግ ሀገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶች ከፀረ ተባይ ኬሚካል ቅሪት ነፃ ሆነው በውጭ ሀገራት ተወዳዳሪ እና ተፈላጊ ከመሆናቸው ባሻገር በከፍተኛ ወጪ የሚመረቱ ምርቶች እንዳይወገዱ ያደርገዋል፡፡

209. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በማስመጣት ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ሳይመዘገቡና ፍቃድ ሳያገኙ እንዳያስተዋውቁ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ቢያደርግ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች መዋል ላለባቸውና ለታለመላቸው አላማ እንዲውል ከማድረጉ በተጨማሪ በዘርፉ ስራ ላይ በህገወጥ መንገድ የተሰማሩ አካላት ወደ ህጋዊ መንገድ ገብተው የፀረ ተባይ ኬሚካል ስራውን የተሳካና የተሳለጠ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡

210. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተገቢው ሁኔታ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋና ተግባራዊ ቢያደርግ በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የፀረ ተባይ ኬሚካል ስራው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን፣ በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ስራዎችን ከኃላፊነትና ከተጠያቂነት አንፃር እንዲያከናውኑ ከማድረጉ በተጨማሪ በህገ ወጥ መንገድ ወደ

ሀገሪቱ የሚገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንዲለዩና ብልሹ አሰራር እንዲወገድ ያደርገዋል፡፡

211. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ያላቸው እና ከተመረቱ 6 ወር ያላለፈባቸው መሆናቸውን በተገቢው ሁኔታ ቢያረጋግጥ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ቀን ድረስ በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ህገ ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካል ዝውውር እና ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እነዳይኖሩ እንዲሁም ለህገ ወጥ የኮንትሮባንድ ንግድ በር እንዳይከፍት እንደሚያደርገው የታመናል፡፡

212. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ስላጣንና ኃላፊነት ተጠቅሞ ክልሎችን፣ የከተማ አስተዳደሮችን እና በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስራውን በብቃት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ጠብቀው ስራዎችን እያከናወኑ ስለመሆናቸው ለውጥ ሊያመጣ በሚያስችል መልኩ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል መዋቅር በማጥናት እና መዋቅሩ የሚጠይቀውን የሙያ ስብጥር ያሟላ የሰው ኃይል እንዲኖረው ቢያደርግ በክትትልና ቁጥጥር ማነስ ምክንያት በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ላይ የሚደረሰውን የግንዛቤ ማነስ፣ የአጠቃቀም ችግሮች፣ የጥራት መጓደሎች እና አላስፈላጊ ህገ ወጥ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዝውውር ለማስቀረትና መጠናቸውን ለመቀነስ ከማስቻሉም በተጨማሪ ችግሮቹ ሲከሰቱ ተጠያቂውን በመለየት አዋጁን መሰረት ያደረገ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ በወቅቱ ለመውሰድ ያስችለዋል፡፡

213. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን እንዲሁም በተዋረድ የዘርፉን ስራ በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት ቢያሟላ በክልሎች፣ በከተማ አስተዳደሮች እና በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው በሚገኙ አካላት የሚደረገውን ክትትልና ቁጥጥር ቀልጣፋና ለውጥ ሊያመጣ የሚያስችል እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

214. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማስገቢያ ፍቃድ አሰጣጥ፣ የማስገቢያ መስፈርቶች እና እንዳይገቡ የሚከለከሉ ፀረ-ተባዮች በቅድሚያ በግልፅ መረጃውን ለተገልጋዩ የሚያሳውቅበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

215. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በእያንዳንዱ የፀረ ተባይ የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አጠቃቀማቸውን

ለመከታተል የሚያስችል የፀረ ተባዮችን ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት፣ በዳታ ቤዝ የተደገፈ መረጃ ቢኖረውና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ቢያደርግ የዘርፉ ስራ በብቃት፣ ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ያደርገዋል፡፡

216. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ ውስጥ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች በአይነትና በመጠን እንዲሁም በቦታ እየተዘረዘሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ቢያደርግ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተበታተነ እና ባልተደራጀ መልኩ እንዳይቀመጡ ያደርገዋል፡፡

217. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት አስተማሪ የሆኑ መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን ቢኖረው ህብረተሰቡና አርሶ አደሩ ለፀረ ተባይ ኬሚካሎች ያለው ግንዛቤ ከፍ እንዲል ከማድረጉ በተጨማሪ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደርገዋል፡፡

218. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አማካሪ ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ በመግባት ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ ቢሰበሰብ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

219. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣አጠቃቀምና ስርጭትን በሚመለከት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

220. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

221. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች መሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

222. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ በማድረግ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋና አፈፃፀሙን

ቢከታተልና ቢቆጣጠር በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ባልተደራጀ እና ባልተሰበሰበ መልኩ ያሉትን ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡

223. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ለሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት እንዲጠበቅ አስፈላጊውን የመከላከያ ትጥቆችን ስለማቅረባቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ቢያደርግ በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በግንዛቤ እና በአጠቃቀም ችግር የሚደርሰውን የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ጉዳት እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡

224. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉና የፅሁፍ ግብረ መልስ ባለመስጠቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው በብቃት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሁም በተሳለጠ መልኩ እንዳይሰራ ያደርገዋል፡፡

225. ማንኛውም አካል ያልታሸገና መለያ ያልተደረገበትን ፀረ ተባይ ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ እንዳያስገባ፣ እንዳያከማች፣ እንዳያጓጉዝ እና ለሽያጭ እንዳያቀርብ ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

226. በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በተለያዩ ሚ/ር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ በሚ/ር መ/ቤቱ በኩል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡

227. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን የሚከታተልበት እና የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

228. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የተሰራላቸው፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳትና ውሃ ከሚገኝበት ቦታ የራቁ ስለመሆናቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

229. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ካሉ መጋዝኑን ወይም የመሸጫ ቦታውን ማሸግ አለበት፡፡


230. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን በቂ፣ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ባለመስጠቱና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው ያለ ግንዛቤ እንዲሰራ ከማድረጉ በተጨማሪ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በእፅዋት እና በአካባቢ ላይ የሚደርሰው ጎጅ ተፅዕኖ ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡

231. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና በዘርፉ የሚሰሩ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ስራው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን በቅንጅት ባለመስራቱና የመግባቢያ ሰነድ

ባለመፈራረሙ እንደ ሀገር የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራው የተሳካና የተሳለጠ እናዳይሆን ከማድረጉም በተጨማሪ ለዘርፉ ትኩረት እንዳይሰጠው ያደርገዋል፡፡

232. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ቆጠራ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መወሰድ ያለበትን እርምጃ መነሻ ሀሳብ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ባለማቅረቡ በሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ቁጥር እንዳይታወቅ ከማድረጉ በተጨማሪ የሚመለከታቸው አካላት ለዘርፉ ያላቸው መረጃ እንዲቀንስ ያደርገዋል፡፡

## አባሪ 1 የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 2 የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት

| የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ | የመመዘኛ መስፈርቶች / Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አመዘጋገብ፣ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና የመረጃ አያያዝ ስርዓቱ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፡፡ | 1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን ለመተግበር የሚያስችለው ደንብ፣ መመሪያ እና እስታንዳርድ ሊያዘጋጅና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| | 1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ደህንነቱንና ጥራቱን በላብራቶሪ መርምሮና አረጋግጦ ሊመዘግብ ይገባል፡፡ |
| | 1.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በግብርና ምርቶች ላይ ሊኖር የሚችል የፀረ-ተባይ ቅሪት መጠን መለየት የሚያስችል አለም አቀፍ እውቅና ያለው ላብራቶሪ ሊኖረውና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በማስመጣት ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ሳይመዘገቡና ፍቃድ ሳያገኙ ሲያስተዋውቁ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት የምዝገባ እና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 1.6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማንኛውም ፀረ ተባይ ኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሰነድ ያላቸው እና ከተመረቱ 6 ወር ያላለፈባቸው ስለመሆናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 1.7 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኘውን የዘርፉን ስራ ሊያሰራ የሚያስችል መዋቅር ሊኖረው እና በመዋቅሩ የተቀመጠውን የሰው ሃይል በስብጥሩ መሰረት ሊያሟላ ይገባል፡፡ |
| | 1.8 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓቱን |

| | |
|---|---|
| | እንዲሁም በተዋረድ የዘርፉን ስራ በተገቢው ሁኔታ ሊያሰራ የሚያስችል ግብዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 1.9 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች ማስገቢያ ፍቃድ አሰጣጥ፣ የማስገቢያ መስፈርቶች እና እንዳይገቡ የሚከለከሉ ፀረ-ተባዮች በቅድሚያ በግልፅ መረጃውን ለተገልጋዩ የሚያሳውቅበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.10 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በእያንዳንዱ የፀረ ተባይ የህይወት ዑደት ደረጃ ውስጥ ያላቸውን እንቅስቃሴና አጠቃቀማቸውን ለመከታተል የሚያስችል የፀረ ተባዮችን ዝርዝርና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የያዘ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት፣ በዳታ ቤዝ የተደገፈ መረጃ ሊኖረው እና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.11 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ ውስጥ በወቅቱ ጥቅም ሊሰጡ ያልቻሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን፣ የተበከሉ ባዶ የፀረ ተባይ መያዣዎች፣ የተበከሉ አፈሮችና ምርቶች በአይነትና በመጠን እንዲሁም በቦታ እየተዘረዘሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 1.12 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት አስተማሪ የሆኑ መልዕክቶች የሚያስተላልፍበት የሚዲያ ሽፋን ሊኖረው እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.13 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ-ተባይ ኬሚካል አማካሪ ቦርድ አቋቁሞ ወደ ስራ ሊገባ እና ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ ሊሰበሰብ ይገባል፣ |
| 2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አጠባበቅ እና አወጋገድ ስርዓቱ ቀልጣፋና | 2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎች አያያዝ፣አጠቃቀምና ስርጭትን በሚመለከት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች በሰው ልጆች፣ በእንስሳት፣ በዕፅዋትና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን ጎጂ ተፅዕኖ መቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| ውጤታማ መሆኑን መገምገም፡፡ | 2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች መሸጥ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙያው የሰለጠኑ እና ብቃት ያላቸው መሆናቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2.4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ለብቻው በአግባቡ በመያዝና አግባብነት ባለው ማጠራቀሚያ በመሰብሰብ ለብቻው በተከለለለት ቦታ በሰው፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት ጤናና አካባቢን በማይጎዳ ሁኔታ ጥበቃ በማድረግ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሚወገድበትን ስርዓት ሊዘረጋ እና አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡ |
| 3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና የኳራንቲን ጣቢያዎችን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የተከሰቱ ችግሮችን በመለየት አስፈላጊውን ግብረ መልስ እየሰጠ ስለመሆኑ መገምገም፡፡ | 3.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ለሰራተኞች የራስ ጤንነትና ደህንነት እንዲጠበቅ አስፈላጊውን የመከላከያ ትጥቆችን ስለማቅረባቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት በታቀደና ተከታታይነት ባለው መልኩ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ስራ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የፅሁፍ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 3.3 ማንኛውም አካል ያልታሸገና መለያ ያልተደረገበትን ፀረ ተባይ ኬሚካል ወደ አገር ውስጥ እንዳያስገባ፣ እንዳያከማች፣ እንዳያጓጉዝ እና ለሽያጭ እንዳያቀርብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3.4 በፀረ ተባይ ኬሚካል ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በተለያዩ ሚ/ር መ/ቤቶች ፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከታለመለት አላማ ውጭ እንዳያውሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከማቸት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ ጥቅም ላይ አለመዋላቸውን የሚከታተልበት እና የሚቆጣጠርበት የአሰራር ስርዓት |

| | |
|---|---|
| | ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፀረ ተባይ ኬሚካል ማከማቻ መጋዝኖች ከመሰራታቸው በፊት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የተሰራላቸው፣ ከሰዎች፣ ከእንስሳትና ውሃ ከሚገኝበት ቦታ የራቁ ስለመሆናቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3.7 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዝኖች ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ ተባይ ኬሚካሎች ካሉ መጋዝኑን ወይም የመሸጫ ቦታውን ሊያሽግ እና ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3.8 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፀረ ተባይ ኬሚካሎች ዙሪያ ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም በዘርፉ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን በቂ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሊሰጥና ለተግባራዊነቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| 4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና ኳራንቲን ጣቢያዎችን እንዲሁም በዘርፉ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትን በመለየት በቅንጅት እየሰራ መሆኑን መገምገም፡፡ | 4.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በሚመለከት ኳራንቲን ጣቢያዎችን፣ ከተማ አስተዳደሮችን፣ ክልሎችን እና በዘርፉ የሚሰሩ ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በመለየት ስራው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆን በቅንጅት ሊሰራና የመግባቢያ ሰነድ ሊፈራረም ይገባል፡፡ |
| | 4.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ቆጠራ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መወሰድ ያለበትን እርምጃ መነሻ ሀሳብ ሊያዘጋጅ እና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያቀርብ ይገባል፡፡ |

## <u>አባሪ 3</u>

## <u>በናሙና የታዩ የከተማ መስተዳደሮች፣ ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ኳራንቲን ጣቢያዎች፣ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅቶች እና በዘርፉ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ዝርዝር</u>

| ተ.ቁ | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ክልሎች | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ዞኖች | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ወረዳዎች | ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ሌሎች አካላት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የከተማ ግብርና ቢሮ | --------------- | ------------- | ✓ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣<br>✓ ለአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፣<br>✓ ቦሌ ካርጎ ኳራንቲን ጣቢያ |
| 2 | ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ | ✓ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ግብርና መምሪያ፣<br>✓ ለደቡብ ጎንደር ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሀብት መምሪያ፣<br>✓ ለማዕከላዊ ጎንደር ዞን ግብርና መምሪያ፣<br>✓ ለባህርዳር የእፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ባለስልጣን፣ | ✓ ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት<br>✓ ለጎዛምን ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት<br>✓ ማዕከላዊ ጎንደር ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት፣ | ✓ ለደብረ ማርቆስ የእፅዋት ዘርና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥርና ኳራንቲን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣<br>✓ መተማ ኳራንቲን ጣቢያ<br>✓ ባህርዳር ኳራንቲን ጣቢያ<br>✓ ጎንደር ኳራንቲን ጣቢያ |
| 3 | ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ | ✓ ለምስራቅ ሸዋ ዞን ግብርና መመሪያ፣<br>✓ ለምዕራብ አርሲ ዞንግብርና መመሪያ፣ | ✓ ለሻሸመኔ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣<br>✓ ለዱግዳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣<br>✓ ለአዳሚ ቱሉ ጂዱ ኮምቦልቻ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣ | ✓ ዝዋይ ሮዝ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅት፤<br>✓ ኤኪው ሮዝ የአበባ እርሻ ልማት ድርጅት፣<br>✓ አዳሚ ቱሉ የፀረ-ተባይ ኬሚካል ማምረቻ ፋብሪካ<br>✓ ይሳከር የግብርና ግብዓት አስመጭ ኃ/የተ/የግ/ድርጅት<br>✓ ለሞጆ ደረቅ ወደብኳራንቲን ጣቢያ<br>✓ አዳማ እፅዋት ኳራንቲን ጣቢያ |
| 4 | ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ | ✓ ሲዳማ ዞን እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ልማት መምሪያ፣ | ✓ ወንዶ ገነት ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት<br>✓ ለሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት | ✓ ግሪን ማርክ ኸርቨስ ኃ/የተ/የግል ማህበር፣ |
| 5 | ትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት | ✓ ለሁመራ ዞን ግብርና መምሪያ | ✓ ለሁመራ ቃፍታ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት | ✓ ሁመራ ኳራንቲን ጣቢያ |